# የሮሜ መልዕክት

## ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንድ ተረጎመው



ተርጓሚ፦ ዲ/ን ይመኑ ተካልኝ

# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሮሜን መልዕክት እንደ ተረጎመው ፦ ይህ ትርጉም የተወሰደው ከ **NPNF first series VOLUME - XI : st john chrysostom : Homily on the Epistle of Rome : translated by Rev . J.B . Morris : edited by Philip schaff** ላይ ነው ።

# መታሰቢያነቱ

"ይህ ታላቅ የትርጉም ሥራ፤ የወርቅ አንደበቱ አባታችን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መለኮታዊ ቃላትን ያፈሰሰባት፣ ዛሬ ግን መብራቷ ተሸፍኖ ለምትገኘው ለቁስጥንጥንያዋ ታላቅ ካቴድራል ለሀጊያ ሶፊያ ፤ የተከበረው የተጋድሎ አክሊል የደፉ ቅዱሳን አባቶቻችን እና እናቶቻችን ማደሪያ ለሆኑት፣ ዛሬ ግን በገዛ አገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ፈተናዎች ጠባቂ እና ሰው አጥተው ለተዘጉ፣ ለፈረሱ እና በመጥፋት ላይ ላሉት ታሪካውያን እና ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት መታሰቢያ ይሁን።ምድራዊው ሕንጻ ቢወሰድም፣ በአባቶቻችን ቃላት ውስጥ ያለው መለኮታዊ እሳት ግን በትውልድ ልብ ውስጥ አይጠፋም!"

ተርጓሚ፦ ዲ/ን ይመኑ ተካልኝ

# ምስጋና

በመጀመሪያ ካለ መኖር ወደ መኖር ላመጣኝ፣ በኃጢአት እና በበደል ሳለሁ በቸርነቱ ታግሦ ለዚህ ታላቅ መንፈሳዊ አገልግሎት አብቅቶኝ፣ ይህንን የወርቅ ድርሳን ተርጉሜ እንድፈጽም በቅዱስ ፈቃዱ የረዳኝ እና ያበረታኝ የቅዱሳን አባቶቻችን አምላክ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር፣ ምስጋና እና ስግደት ዛሬም ዘወትርም እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ ይሁን፤ አሜን።

በመንፈሳዊው ጉዞዬ እና በዚህ ከባድ የትርጉም ሥራ ላይ የእናትነቷ ፍቅር ሳይለየኝ፣ በደካማነቴ እና በሰነፍነቴ ጊዜ ሁሉ በአማላጅነቷ እና በእናትነቷ ላልተለየችኝ፣ የባሕርያችን መመኪያ ለሆነችው ለክብርት እመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የከበረ ምስጋና ይድረሳት።ይህንን መጽሐፍ ስተረጉም በቃላቱ ውስጥ ባለው በሰማያዊ ምስጢር እና በመለኮታዊ እሳት ሕሊናዬን ላበራልኝ፣ በቅዱስ ጳውሎስ ልብ ውስጥ የነበረውን ፍቅር በረቀቀ ጥበቡ ለገለጸልኝ እና በመንፈሳዊ አባትነቱ ለረዳኝ፣ ለዚህ ታላቅ መጽሐፍ ባለቤት የወርቅ አንደበት ለሆነው ለአባቴ ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ምስጋናዬ ከበረከቱ ጋር ይሁን።የዕውቀትን በር ለከፈቱልኝ፣ በመንፈሳዊው የዕውቀት ማዕድ እና በሊቃውንቱ ሥርዓት ኮትኩተው ላሳደጉኝ፣ ለዕድሜ ልክ አርአያዬ ለሆኑት ለውድ መምህሬ ለየኔታ ሊቀ ጠበብት ቆሞስ መሪጌታ እውነቱ ይሁን ውድ ምስጋናዬ እና አክብሮቴ ይድረሳቸው።ገና ከሕፃንነቴ ጀምራ በጸሎቷ እና በእንባዋ የጠበቀችኝ፣ ዛሬ ለደረስኩበት መንፈሳዊ ማዕረግ እና ክብር መሰረት ለሆነችኝ፣ ፍቅሯና ቸርነቷ

በሕይወቴ ሁሉ ለከበበኝ ለውድ እናቴ ለወ/ሮ ዘሪቱ ዋዳ ፍጹም ምስጋና ይሁን።

በዚህ ከባድ የሥራ መድረክ ላይ ከጎኔ ቆማ ብርታት ለሆነችኝ ለውድ እህቴ፤ እንዲሁም በመንፈሳዊ አገልግሎት እና በሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ሁሉ እውነተኛ ደጋፊ እና ወንድም ለሆነኝ ለታማኝ ጓደኛዬ ለዲያቆን አዲሱ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው። በመጨረሻም፣ ይህንን መጽሐፍ በጉጉት ለምትጠባበቁ፣ በጸሎታችሁና በበጎ አሳባችሁ ሁሉ አብራችሁኝ ለቆማችሁ፣ ይህ መለኮታዊ ቃል ለደረሳችሁና ለምታነቡት ለመላው የክርስቶስ ቤተሰቦች ለሆናችሁ ለሕዝበ ክርስቲያን በሙሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው። እግዚአብሔር ሁላችሁንም ይባርክ አሜን ።



# ማውጫ

መግቢያ ..................

ድርሳን አንድ ..............

ድርሳን ሁለት ..............

ድርሳን ሦስት ..................

ድርሳን አራት ..................

ድርሳን አምስት ..................

ድርሳን ስድስት ..................

ድርሳን ሰባት……………….

ድርሳን ስምንት ……………….

ድርሳን ዘጠኝ……………….

ድርሳን አስር ……………….

ድርሳን አሥራ አንድ………….

ድርሳን አሥራ ሁለት………….

ድርሳን አሥራ ሦስት ………….

ድርሳን አሥራ አራት………….

ድርሳን አሥራ አምስት ..........

ድርሳን አሥራ ስድስት ..........

ድርሳን አሥራ ሰባት..............

ድርሳን አሥራ ስምንት ..........

ድርሳን አሥራ ዘጠኝ .............

ድርሳን ሃያ..................

ድርሳን ሃያ አንድ..................

ድርሳን ሃያ ሁለት..................

ድርሳን ሃያ ሦስት..................

ድርሳን ሃያ አራት..................

ድርሳን ሃያ አምስት .............

ድርሳን ሃያ ስድስት .............

ድርሳን ሃያ ሰባት..................

ድርሳን ሃያ ስምንት ..........

ድርሳን ሃያ ዘጠኝ.............

ድርሳን ሰላሳ..................

ድርሳን ሰላሳ አንድ.............

ድርሳን ሰላሳ ሁለት...........

# መግቢያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

በክርስቶስ ኢየሱስ የተወደዳችሁና በክቡር ደሙ የተዋጀችሁ የዚህ መጽሐፍ አንባቢያን ሆይ! ይህ አሁን በእጃችሁ የያዛችሁት መጽሐፍ ተራ የሰው ልጅ የጥበብ ፍልስፍና ወይም የቃላት ድርድር የሰፈረበት ምድራዊ ሰነድ አይደለም። ይልቁኑ የሐዋርያት አለቃ በሆነው በቅዱስ ጳውሎስ ልብ ውስጥ ይነድ የነበረው መለኮታዊ እሳት፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ «የወርቅ አንደበት» ተብሎ በሚጠራው በታላቁ ሊቅና አባት በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አማካኝነት ፈስሶ የቀረበበት ሕያው የቅድስና ምንጭ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የጻፈው መልእክት በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል እንደ ማኅተም የሚቆጠር፣ የክርስትናን እውነተኛ ዶክትሪን (የሃይማኖት መሠረት)፣ የምስጢረ ሥጋዌን ጥልቀት፣ የጸጋን ታላቅነትና በሕግና በእምነት መካከል ያለውን ምስጢር በስፋት የሚተነትን የነገረ መለኮት ቁንጮ ነው። ይህንን ታላቅ የሐዋርያውን ልብ ደግሞ ልክ እንደ እርሱ በክርስቶስ ፍቅር እንደ እብድ ከሆነውና በቅድስና ሕይወት ከበሰለው ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በቀር ማንም ሊፈታውና ሊያብራራው አይችልም ነበር። ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህንን የሮሜን መልእክት በሚተረጉምበት ጊዜ፣ መልእክቱን ያነበውና ያጠናው ብቻ አልነበረም፤ ይልቁኑ በጸሎትና በትጋት ከቅዱስ ጳውሎስ መንፈስ ጋር ይገናኝ እንደነበር ታሪኩ ያስረዳናል። ለዚህም ነው በእነዚህ ሰላሳ ሁለት ድርሳናት ውስጥ

የምናገኘው ትርጉም ተራ ማብራሪያ ሳይሆን፣ የሰማይ ምስጢር በምድር ላይ የተገለጠበት መለኮታዊ ጮኸት የሆነው።

## የአጠቃላይ ድርሳናቱ ይዘትና መዋቅር (ከድርሳን ፩ እስከ ፴፪)

ይህ የትርጉም ሥራ ከሮሜ ምዕራፍ ፩ እስከ ምዕራፍ ፲፮ ያሉትን የሐዋርያውን ቃላት በሰላሳ ሁለት ክፍሎች (ድርሳናት) ከፍሎ በዝርዝር ያብራራል። ሊቁ የአንባቢውን ሕሊና ደረጃ በደረጃ ወደ ሰማያዊው ምስጢር ለመውሰድ ድርሳናቱን በሦስት ዋና ዋና መንፈሳዊ ምሰሶዎች ላይ ይገነባቸዋል፦

### ፩. የሰው ልጅ ውድቀትና የእግዚአብሔር ጸጋ (ከምዕራፍ ፩ — ፰)

በመጀመሪያዎቹ ክፍሎች ሐዋርያው የሰውን ልጅ አጠቃላይ የኃጢአት ቁስልና ውድቀት ይዳስሳል። አሕዛብም ሆኑ አይሁድ በገዛ ፈቃዳቸው ከእግዚአብሔር ሕግ ወጥተው እንዴት ለሞትና ለጥፋት እንደተዳረጉ ያሳያል። የኦሪት ሕግ ሰውን ከኃጢአት ቁስሉ ሊፈውሰው እንዳልቻለ፣ ይልቁኑ ቁስሉን አጉልቶ እንዳሳየው ይተነትናል። እዚህ ላይ ነው ሊቁ የክርስቶስን የማዳን ሥራ (ምስጢረ ሥጋዌን) በታላቅ ግርማ የሚያበስረው። ሰው በኦሪት ሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመንና በከበረው ደሙ አማካኝነት ያለ ዋጋ እንደሚጸድቅ፣ ከባርነት ወጥቶ የእግዚአብሔር የጸጋ ልጅ እንደሚሆን በምዕራፍ ስምንት ላይ በታላቅ የደስታ ድምፅ ያበስረናል።

### ፪. የእግዚአብሔር እውነተኛ ፍትሕና ባለቤትነት (ከምዕራፍ ፱ — ፲፩)

በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ አይሁድ ሕዝብ አለማመንና ስለ አሕዛብ መጠራት የተናገረውን አስቸጋሪ ምስጢር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ልክ እንደ እውነተኛ ሐኪም በጥንቃቄ ይፈታዋል። እግዚአብሔር ሰውን በግድ እንደማያድን፣ ነገር ግን የእያንዳንዱን ሰው ነፃ ፈቃድ እንደሚያከብር ያሳያል። እግዚአብሔር ፍጹም ጻድቅና ፍጹም መሐሪ አምላክ መሆኑን፣ ፍጥረትን ሁሉ የገዛው በገዛ ደሙ በመሆኑ በእኛ ላይ ፍጹም ባለቤትነት እንዳለው ያረጋግጣል።

## ፫. የክርስቲያን የዕለት ተዕለት ቅድስናና ፍቅር (ከምዕራፍ ፲፪ — ፲፮)

በመጨረሻዎቹ ድርሳናት ውስጥ ሊቁ ትምህርቱን (ዶክትሪኑን) ወደ ተግባራዊ የሕይወት ተጋድሎ ያመጣዋል። አንድ ክርስቲያን በምድር ላይ ሲኖር ራሱን እንዴት «ሕያው መስዋዕት» አድርጎ ማቅረብ እንዳለበት፣ ለባለሥልጣናት ስላለው መገዛት፣ ስለ ወንድማማችነት ፍቅርና ስለ እውነተኛ ትሕትና ይመክራል።

በተለይም በእምነት ጠንካራ የሆኑት ወገኖች በእምነት ደካማ የሆኑትን ወንድሞቻቸውን እንዴት በፍቅርና በትዕግሥት ሊይዟቸው እንደሚገባ፣ ሌላውን ሰው ማሰናከልና መናቅ በፈራጁ በክርስቶስ ፊት እንዴት ያለ ታላቅ ቅጣት እንደሚያስከትል፣ እንዲሁም ሊመጣ ስላለው አስፈሪው የገሃነም እሳትና ስለ ጻድቃን የዘላለም አክሊል በመጨረሻዎቹ ክፍሎች ላይ ሕሊናን በሚያናውጥ ኃይለኛ ቃል ያስተምራል።

[የዚህ መጽሐፍ ልዩ ጠባያት እና ማራኪነት]

ይህንን መጽሐፍ አንብቦ የሚጨርስ ሰው እንዲሁ ዕውቀትን ብቻ አግኝቶ አይወጣም፤ ይልቁኑ ሙሉ ማንነቱ ተለውጦና ተቀይሮ ይወጣል። የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የአተረጓጎም ስልት የሚከተሉት ልዩ ውበቶች አሉት፦

የሥነ-ልቦና ጥበብ (Hyperbole)፦ ሊቁ ሐዋርያው ጳውሎስ ሰዎችን በቀጥታ ተቆጥቶ እንዳያሰናክላቸው ሲል፣ እንዴት ጠንካራውን እየገሠጸ ደካማውን በስውር እንደሚያክመው የረቀቀውን የሐዋርያውን ጥበብ ፍንትው አድርጎ ያሳየናል።

በታሪክ የተደገፈ እውነት፦ እግዚአብሔር መሐሪ ብቻ ሳይሆን ጻድቅ ፈራጅም መሆኑን ለማሳየት፣ የኖኅን የውኃ አይኅ፣ የሰዶምና ገሞራን ጥፋት፣ የኢየሩሳሌምን መፈራረስና የጆሴፈስን የታሪክ መጻሕፍት እየጠቀሰ ፍጹም ማምለጫ የሌለውን መለኮታዊ ፍርድ በተጨባጭ ያስረዳል።

የጸሎትና የምስጋና ማኅተም፦ሊቁ እያንዳንዱን ድርሳን ዝም ብሎ በሃሳብ አይዘጋውም፤ ይልቁኑ አንባቢውን ወደ ንስሐና ወደ አምልኮ በመጥራት፣ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ በሚቀርብ ታላቅ የጸሎትና የምስጋና ማዕበል ያሳርገዋል።

## ለአንባቢ የተላለፈ መንፈሳዊ ጥሪ

ውድ አንባቢ ሆይ! ይህንን መጽሐፍ ስታነብ በቸልተኝነትና እንዲሁ የታሪክ መጽሐፍ እንደማንበብ እንዳይሆን ተጠንቀቅ። እያንዳንዱን መስመር ስታነብ ቅዱስ ጳውሎስ በዓይነ ሥጋህ ፊት ቆሞ እንደሚናገርህ፣ የወርቅ አንደበቱ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በጆሮህ ላይ ምስጢሩን እንደሚያንሾካሹክልህ አድርገህ በታላቅ ፍርሃትና ክብር ይዘህ አንብበው። ይህ መጽሐፍ በውስጣችን ያለውን የጥርጣሬ ደመና የሚገፍ፣ በእምነት እንድንጸና የሚያደርግ፣ ከመንፈሳዊ መዛልና ስንፍና ቀስቅሶ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያሻግር ሕያው መመርያ ነው። የቅዱስ ጳውሎስ እረኛነት፣ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጸሎትና በረከት፣ የሁላችን ጌታና መድኃኒት የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ፍቅር ይህንን መጽሐፍ በሚያነቡትና በሚተረጉሙት ሁሉ ላይ ለዘለዓለሙ ይደር፤ አሜን።

# ድርሳን አንድ ( Homily I )

ሮሜ ፩፡፩ "ከኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ሊሆን የተጠራ ሐዋርያም ሊሆን የተለየ የእግዚአብሔር ወንጌል አገልጋይ ጳውሎስ፤ በቅዱሳን መጻሕፍት በነቢያቱ አስቀድሞ ተስፋ የሰጠው።"

ሙሴ አምስቱን መጻሕፍት (ኦሪትን) ሲጽፍ፣ የትም ቦታ ላይ የገዛ ስሙን አልጠቀሰም። ከእርሱ በኋላ የታሪክ መጻሕፍትንየጻፉትም ቢሆኑ ስማቸውን አላስገቡም። ማቴዎስም ቢሆን፣ ዮሐንስም፣ ማርቆስም ወይም ሉቃስም ቢሆኑ እንዲሁ ስማቸውን አልጻፉም። ብፁዕ ጳውሎስ ግን በሁሉም መልዕክቶቹ ላይ ስሙን ያስቀምጣል። ይህ ለምን ሆነ? እነርሱ (ወንጌላውያኑ)የጻፉት በፊታቸው ለነበሩ ሰዎች (በአካል ለሚያውቋቸው) ነበር፤ በአካል እያሉ ደግሞ ማንነታቸውን መግለጽ አላስፈላጊ ነበርና። ይህ ሰው (ጳውሎስ) ግን ጽሑፎቹን የላከው ከሩቅ ሐገርና በመልዕክት (በደብዳቤ) መልክ ስለነበረ፣ ስሙን መጨመሩ አስፈላጊ ነበር። በዕብራውያን መልዕክት ላይ ግን ይህንኑ (ስሙን መጥቀስ) ካላደረገ፣ ይህም ቢሆን ከእርሱጥበበኛ ውሳኔ የተነሳ ነው። ምክንያቱም (ዕብራውያን) በእርሱ ላይ ቅሬታ ስለነበራቸው፣ ገና በመጀመሪያ ስሙን ሲሰሙ ለትምህርቱ የሚሰጡትን በር እንዳይዘጉ፣ ስሙን በመሰወር ትኩረታቸውን በብልሃት ለማግኘት ሲል ነው። ነገር ግን አንዳንድ ነቢያትና ሰለሞን ስማቸውን አስፍረው ከሆነ፣ አንዳንዶቹ ለምን ስማቸውን ማስፈር እንደፈለጉ ሌሎች ደግሞ ለምን እንዳልፈለጉ ወደፊት

እንድትመረምሩት ለእናንተ እተወዋለሁ። ምክንያቱም ሁሉንም ነገር ከእኔ ልትማሩ አይገባም፤ ይልቁንም አእምሯችሁ፡ሰነፍ እንዳይሆን እናንተም ደክማችሁ እንድትመረምሩ ይገባል።

**"የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ"**

እግዚአብሔር ሳውል የነበረውን ስሙን ለምን ወደ ጳውሎስ ቀየረው? ይህም በዚህ ረገድ እንኳን ከሐዋርያት እንዳያንስ ነው፤ ይልቁንም የደቀ መዛሙርት አለቃ (ቅዱስ ጴጥሮስ) የነበረውን ያንን ብልጫ እርሱም እንዲያገኝ **(ማርቆስ ፫፥፲፮)**፣ እንዲሁም ከእነርሱ ጋር ይበልጥ የተቀራረበ አንድነት እንዲኖረው ነው። ራሱንም "የክርስቶስ ባሪያ" ብሎ ይጠራል፤ ነገር ግን ይህንን ብቻ አይደለም። ምክንያቱም ብዙ ዓይነት ባርነቶች (አገልጋይነቶች) አሉና። አንደኛው ከፍጥረት የተነሳ ነው፤ በዚህም መሠረት መጽሐፍ፦ **"ሁሉ ባሪያዎችህ ናቸውና" (መዝሙር ፻፲፱፥፺፩)** ይላል። እንደዚሁም (መጽሐፍ) 'ባሪያዬ ናቡከደነጾር' (ኤር. ፳፭፥፱) እንደሚል፤ ሥራ ሁሉ ለፈጣሪው ባሪያ ነውና። ሌላው የባርነት ዓይነት ደግሞ ከእምነት የሚገኝ ነው፤ ስለ እርሱም እንዲህ ይላል፦ 'ነገር ግን አስቀድማችሁ የኃጢአት ባሪያዎች ከሆናችሁ በኋላ ለተሰጣችሁለት ለትምህርት ዓይነት ከልባችሁ ስለ ታዘዛችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፤ ከኃጢአትም አርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ባሪያዎች ሆናችኋል።' (ሮሜ ፮፥፲፮-፲፰) ሌላኛው ደግሞ ከሕዝባዊ ተገዥነት የሚመጣ ነው፤ በዚህም መሠረት 'ባሪያዬ ሙሴ ሞተ' (ኢያሱ ፩፥፪) ይላል። በእርግጥ አይሁድ ሁሉ ባሪያዎች ነበሩ፤ ሙሴ ግን በማኅበረሰቡ መካከል ደምቆ በመታየቱ በልዩ ሁኔታ 'ባሪያ' ተባለ።

እንግዲህ ጳውሎስ በእነዚህ ሁሉ አስደናቂ የባርነት ዓይነቶች ባሪያ ስለሆነ፣ ይህንኑ "'የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ'" በማለት ከሁሉ በላይ እንደሆነ የክብር ስም አድርጎ አቀረበው። ስለ ቤዛነት ሥራው የሚገልጹትን ስሞችም ከታችኛው ወደ ላይኛው ከፍ እያደረገ ያስቀምጣቸዋል። "ኢየሱስ" የሚለው ስም መልአኩ ከድንግል ይጸነስ ዘንድ ከሰማይ የመጣበት ስም ነው፤ "ክርስቶስ" የተባለው ደግሞ ከመቀባቱ (ከመቀደሱ) የተነሳ ሲሆን፣ ይህም ራሱ ከሥጋ ጋር የተያያዘ ነው። "በምን ዓይነት ዘይትስ ተቀባ ?" የሚል ጥያቄ ቢነሳ፤ የተቀባው በዘይት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ነው[1]። መጽሐፍም መንፈስ ቅዱስ በቅብዓት ውስጥ ዋናው ነጥብ በመሆኑና ዘይቱም ለዚሁ ተግባር የሚውል በመሆኑ፣ እንዲህ ያሉትን ቅቡዕ ብሎ የመጥራት ልማድ አለው። ታዲያ በዘይት ያልተቀቡትን ቅቡዓን ብሎ የት ቦታ ጠራ? "የቀባኋቸውን አትንኩ፥ በነቢያቶቼም ክፉ አታድርጉ" (መዝ. ፻፭፥፲፭) ይላል፤ በዚያን ጊዜ ግን በዘይት የመቀባት ሥርዓት ገና አልተጀመረም ነበር።

## "ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ"

በሁሉም መልዕክቶቹ ላይ ራሱን 'የተጠራ' ብሎ ይጠራል። ይህም የራሱን የዋህነት (ቅንነት) ለማሳየት ነው፤ ይህም ማለት ሐዋርያነትን የፈለገው እርሱ ራሱ ሳይሆን፣ ሲጠራው ቀርቦ የታዘዘ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ምዕመናንንም "'ቅዱሳን ለመሆን

---

[1] ሊቁ «ክርስቶስ» የሚለውን ስም ትርጉም ሲያብራራ፣ ስሙ በቀጥታ ከሥጋቄው (ሰዋዊ ባሕርይን ከመንሳቱ) ጋር የተያያዘ መሆኑን ያስገነዝባል። ጌታችን «ክርስቶስ» (ተቀባ) የተባለው በብሉይ ኪዳን እንደነበሩት ነገሥታትና ካህናት በቁሳዊ ዘይት ስለተቀባ ሳይሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ ስለተቀባ (ስለተቀደሰ) ነው።
አንባቢው እዚህ ላይ «ዘይት በሌለበት እንዴት ቅብዓት ሊባል ይችላል?» የሚል ጥያቄ እንዳያነሳ፣ ሊቁ የመዝሙር 105፥15ን ጥቅስ («ቅቡዓኖቼን አትንኩ») በማስረጃነት ይጠቅሳል። የብሉይ ኪዳን አባቶች (አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ) በዘይት የመቀባት ሥርዓት ገና ሳይጀመር «ቅቡዓን» መባላቸው፣ እውነተኛው ቅብዓት የቁሳዊ ዘይት መኖር ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ቅድስና መሆኑን ለማሳየት ነው።
ስለዚህ የሊቁ ቀጥተኛ መልዕክት፦ «የክርስቶስ ቅብዓት በቁሳዊ ዘይት ሳይሆን፣ እርሱ በሥጋ በተገለጠ ጊዜ ሥጋው ከመለኮት ጋር በተዋሐደበት ቅጽበት በመንፈስ ቅዱስ የተፈጸመ መለኮታዊ ቅድስና ነው» የሚል ነው።

የተጠሩ" ይላቸዋል፤ እነርሱ አማኞች እንዲሆኑ እስከመጠራት ድረስ ቢደርሱም፣ በእርሱ እጅ ላይ ግን ከዚህ የተለየ ነገር አደራ ተሰጥቶታል፤ እርሱም ሐዋርያነት ነው። ይህም ስፍር ቁጥር የሌላቸው በረከቶች የሞሉበት፣ ከስጦታዎችም ሁሉ የሚበልጥና ሁሉንም የሚያጠቃልል ነው። ስለዚህ ጉዳይ (ስለ ሐዋርያነት) ከዚህ በላይ ምን ሊባል ይችላል? ክርስቶስ በአካል በነበረ ጊዜ ያደርገው የነበረውን ሁሉ፣ ሲሄድ በእነርሱ እጅ አደራ ሰጥቷቸዋል። ይህም ጳውሎስ ስለ ሐዋርያነት ክብር ከፍ አድርጎ ሲናገር እንዲህ ብሎ ይጮኻል፦ "እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን" (፪ ቆሮ. ፭÷፳)፤ ይህም ማለት "በክርስቶስ ምትክ" ማለት ነው።

### "ለእግዚአብሔር ወንጌል የተለየ"

በአንድ ቤት ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ለተለያዩ ሥራዎች እንደሚለይ፣ እንዲሁ በቤተክርስቲያንም ውስጥ ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍፍሎች አሉ። በዚህም አባባሉ እርሱ የተሾመው በዕጣ ብቻ ሳይሆን፣ ከጥንት ጀምሮ ከመጀመሪያውም ለዚህ አገልግሎት አስቀድሞ ተወስኖ (ተለይቶ) እንደነበር ለእኔ የሚጠቁመኝ ይመስላል። ይህም ነጥብ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ላይ፦ "በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ" (ሐዋ. ፲፫÷፪) በማለት መንፈስ ቅዱስ እንደተናገረ ሲገልጽ ያረጋገጠው ነው። 'ለተለየ' ሲልም፣ ለጋራ ሥራ ከተጠሩት መካከል ለዚሁ ተግባር የተመረጠ መሆኑን ያሳያል። "ወንጌል" የሚለውን ቃል ሲጠቀም ደግሞ፣ የአይሁድን ትኩረት ለማግኘትና በአእምሯቸው ያለውን የነገሮች ስሜት ለመለወጥ ነው። 'ምን ማለትህ ነው?' ብለው ቢጠይቁት፦ 'ነገሮች ሁሉ የሚያበቁና ወደ ፍጻሜ

የሚመጡ ይመስላችኋል? አይ፣ እነዚህ (የምነግራችሁ) ነገሮች ከድሮዎቹ ይልቅ እጅግ የተሻሉና የሚያስደስቱ ናቸው' ለማለት ነው። ምክንያቱም ወንጌል (የምስራች) የሚባለው መልካም ነገር እንጂ የሚያሳዝን ነገር አይደለምና። ደግሞም 'የእግዚአብሔር' ወንጌል በማለት ስሙን ይጠራል። ይህም የአይሁድን አእምሮ ለማለስለስና ትኩረታቸውን ለመሳብ ነው። ምክንያቱም እርሱ ስለ አብ የሚሰብክ መስሎ ሲታይ፣ እነርሱም ለመስማት ይበልጥ ዝግጁ ይሆናሉና።

## በቅዱሳን መጻሕፍት በነቢያቱ አስቀድሞ ተስፋ የሰጠው።

ይህንን ያመጣው ለምንድን ነው? "ወንጌሉ አዲስና እንግዳ ነው" ብለው እንዳይከሱት ነው። ምክንያቱም አይሁድ አዲስ ለሆኑ ነገሮች (ፈጠራዎች) እጅግ ጥንቃቄ ያደርጉና ይጠራጠሩ ነበር። ስለዚህ ወንጌሉ ጥንታዊ መሆኑንና በነቢያትም አስቀድሞ የተነገረለት መሆኑን በማሳየት፣ የሰማያትንና የምድርን ጌታ (እግዚአብሔርን) ምስክር አድርጎ ያቀርባል። መጽሐፍትንም ምስክር ያደርጋል። ነገር ግን 'መጽሐፍት' ብቻ ብሎ አላበቃም፤ 'ቅዱሳን መጻሕፍት' አላቸው እንጂ። ምክንያቱም ንግግሩ (ወንጌሉ) ከመጻሕፍት ብቻ ሳይሆን፣ ቅዱሳን ከሆኑት ከመንፈስ ቅዱስ መጻሕፍት የመጣ መሆኑን ለማሳየት ነው።

ከዚህም በኋላ፦

## "ስለ ልጁ (ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ)"

ይላል። ተመልከት፣ የወንጌሉን ዋና ሐሳብ እንዴት አድርጎ በአጭሩ እንደጨመቀው! ወንጌል ማለት ስለ 'ልጁ' የሚነገር ነውና። 'ልጁ' የሚለው ቃል ደግሞ የእርሱን (የክርስቶስን)

ባሕርይና ማንነት የሚገልጽ ነው። ለመስማት ፈቃደኛ የሆኑት ሰምተውታል። እርሱም (ጌታ) እንዲህ ይላል፦ "አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሴት አደረገ፥ አየም ደስም አለው" (ዮሐንስ ፰፥፶፮)።

ታዲያ እንዴት "እናንተ የምታዩትን ያዩ ዘንድ ብዙዎች ነቢያት ተመኝተው አላዩም" (ማቴ. ፲፫፥፲፯) ይላል? ይህ ማለት ግን እንደ እናንተ በአካል ፊት ለፊት ሥጋውንና የሚያደርጋቸውን ተአምራት አላዩም ማለት ነው። ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ከስንት ዘመን በፊት አስቀድመው እንደተነገሩ እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን በግልጽ ሊያደርግ ሲል፣ ሰዎች በደረሰ ጊዜ እንዲቀበሉት ለማለማመድ ከረጅም ጊዜ በፊት ያውጃቸዋል። "በቅዱሳን መጻሕፍት" ምክንያቱም ነቢያት የተናገሩትን ብቻ ሳይሆን የተናገሩትንም ጽፈዋል፤ መጻፍ ብቻም ሳይሆን በተግባርም ጥላ አድርገው አሳይተውታል። ለምሳሌ አብርሃም ይስሐቅን በሰዋ ጊዜ፣ ሙሴ እባቡን በሰቀለ ጊዜ፣ በአማሌቅ ላይ እጆቹን በዘረጋ ጊዜና የፋሲካውን በግ ባቀረበ ጊዜ ሁሉ አምሳል ሆነው አልፈዋል ።

### ቁጥር ፫፦ "በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ ስለ ልጁ።"

አንተ ጳውሎስ ሆይ! ነፍሳችንን እንዲህ ከፍ ካደረግህና ካነቃቃህ በኋላ፣ እንዲሁም ሊነገሩ የማይችሉ ታላላቅ ነገሮችን ካሳየኸን በኋላ፣ ስለ ወንጌል ያውም ስለ እግዚአብሔር ወንጌል ከተናገርህና የነቢያትን ማኅበር ካመጣህ በኋላ፣ እነርሱም ብዙ ዓመታት በፊት ስለሚመጡት ነገሮች አውጅው እያለህ፤ ለምን እንደገና ወደ ዳዊት ታወርደናለህ? ንገረኝ እስኪ! የምታወራው ስለ አንድ ተራ ሰው ነውን? ወይስ የእሰይን ልጅ አባት ልታደርገው ነው? ይህስ

አሁን ካልከው ከፍ ያለ ነገር ጋር እንዴት ይመጣጠናል? አዎን! ሙሉ በሙሉ ይመጣጠናል። ምክንያቱም ንግግራችን ስለ አንድ ተራ ሰው አይደለምና። "በሥጋ" የሚለውን ቃል የጨመርኩትም ለዚህ ነው፤ ይህም ለዚሁ አካል (ለክርስቶስ) ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ሌላ ልደት እንዳለው ለመጠቆም ነው።

ታዲያ ለምን ከዚያ (ከመለኮታዊ ልደቱ) ሳይሆን ከዚህ (ከሥጋዊ ልደቱ) ጀመረ? ማቴዎስ፣ ሉቃስና ማርቆስም የጀመሩት ከዚሁ ስለሆነ ነው። ሰዎችን በእጃቸው ይዞ ወደ ሰማይ የሚመራ ሰው፣ የግድ ከታች ወደ ላይ ሊመራቸው ይገባልና። ትክክለኛው የድኅነት ሥራ ቅደም ተከተልም እንደዚሁ ነበረ። በመጀመሪያ በምድር ላይ ሰው ሆኖ አዩት፤ ከዚያም አምላክ መሆኑን ተረዱ። እንግዲህ ጌታ ራሱ ትምህርቱን በሰላበት በዚያው አቅጣጫ፣ ደቀ መዝሙሩም (ጳውሎስ) ወደዚያ የሚመራውን መንገድ ቀረጸ። ስለዚህ "በሥጋ" የሚለው ልደት በንግግሩ ውስጥ ቀድሞ የተቀመጠው፣ እርሱ መጀመሪያ ስለሆነ ሳይሆን፣ ሰሚውን ከዚህ ተነስቶ ወደዚያ (ወደ መለኮታዊው) እንዲመራው ስለፈለገ ነው።"

ቁጥር ፬፦ "እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሳ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተገልጦአል፤ እርሱምጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።"

እዚህ ላይ የተነገረው ሐሳብ በቃላቱ መጠቅለል (መጠጋጋት) የተነሳ ግልጽነት ይጎድለዋል፤ ስለዚህ ለይቶ ማየት ያስፈልጋል። ለመሆኑ ምንድን ነው የሚለው? እኛ የምንሰብከው ከዳዊት የተወለደውን እርሱን ነው ይላል። ይህ ግልጽ ነው። ታዲያ ይህ ሥጋ የለበሰ "አካል" የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በምን ይታወቃል? አንደኛ፦ በነቢያት የታወቀ ነው፤ ስለሆነም "በቅዱሳን መጻሕፍት

በነቢያቱ አስቀድሞ ተስፋ የሰጠው" (ቁ. ፪) ይላል። ይህ የማስረጃ መንገድ ደካማ አይደለም።

ሁለተኛ፦ ከተወለደበት መንገድ የታወቀ ነው፤ ይህም "በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ" በማለት የገለጸው ነው፤ ምክንያቱም የተፈጥሮን ሕግ ጥሶ (ያለ ወንድ ዘር) ተወልዷልና። ሦስተኛ፦ ካደረጋቸው ተአምራት የታወቀ ነው፤ ይህም ትልቅ ኃይልን የሚያሳዩ ናቸው፤ "በኃይል" ማለቱም ይህንን ነው። አራተኛ፦ በእርሱ ለሚያምኑት ከሰጠው መንፈስ የታወቀ ነው፤ በእርሱም አማካኝነት ሁሉንም ቅዱሳን አድርጓቸዋል፤ ስለሆነም "እንደ ቅድስና መንፈስ" ይላል። እንዲህ ያሉ ስጦታዎችን መስጠት የእግዚአብሔር ብቻ ነውና። አምስተኛ፦ በትንሣኤው የታወቀ ነው፤ ምክንያቱም መጀመሪያና እርሱ ብቻውን ራሱን አስነስቷልና። ይህ ራሱ ያለ እፍረት ለሚከራከሩት ሰዎች እንኳን አፋቸውን ለመዝጋት በቂና ከሁሉ በላይ የሆነ ተአምር መሆኑን ጌታ ተናግሯል።

"ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም አነሳዋለሁ" (ዮሐ. ፪፥፲፱) እንዳለ፤ ደግሞም "የሰውን ልጅ ከምድር ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ እኔ እርሱ እንደሆንሁ ታውቃላችሁ" (ዮሐ. ፰፥፳፰)፤ እንዲሁም "ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም" (ማቴ. ፲፪፥፴፱) ብሏል። ታዲያ "ተገልጦአል" ማለት ምን ማለት ነው? በሁሉም ሰው ስሜትና ምስክርነት የታየ፣ የተገለጠ፣ የተፈረደበትና የታመነበት ማለት ነው፤ ይህም በነቢያት፣ በሥጋ በሆነው አስደናቂ ልደቱ፣ በተአምራቱ ውስጥ በነበረው ኃይል፣

ቅድስናን በሰጠበት መንፈስና የሞትን አምባገነንነት ባቆመበት በትንሣኤው የተረጋገጠ ነው።

ቁጥር ፭፦ "በእርሱም ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሳ መታዘዝ ይሆን ዘንድ ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን።"

የባሪያውን (የጳውሎስን) ቅንነት ተመልከት። ምንም ነገር የእኔ ይሁን አይልም፤ ይልቁንም ሁሉንም የጌታው ያደርገዋል። በእርግጥ ይህንን የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህም ጌታ እንዲህ አለ፦

"የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" (ዮሐ. ፲፮፥፲፪)፤ ደግሞም "በርናባስንና ሳውልን... ለዩልኝ" (ሐዋ. ፲፫፥፪) ይላል። ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልዕክትም "ለአንዱ በመንፈስ..." ይላል ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋል፥ ለሌላውም እውቀትን መናገር በዚያው መንፈስ ይሰጠዋል' (፩ ቆሮ. ፲፪፥፰፡፲፩)፤ ያም መንፈስ እንደ ወደደ ለእያንዳንዱ ያካፍላል። በሚሊጢን ያሉትን (የኤፌሶን ቀሳውስትን) ሲያነጋግራቸውም፦ 'መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት...' ይላል (ሐዋ. ፳፥፳፰)።

ተመልከት፤የመንፈስ ቅዱስ የሆነውን የልጁ (የክርስቶስ) እንደሆነ፣ የልጁ የሆነውን ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። 'ጸጋንና ሐዋርያነትን'፤ ይህም ማለት ሐዋርያት እንድንሆን እኛ ለራሳችን ያሳካነው ነገር አይደለም። ይህ ክብር የተሰጠን እኛ እጅግ ደክመንና ለፍተን ስላገኘነው ሳይሆን፣ ጸጋን ተቀበልን፤ የተገኘውም ስኬታማ ውጤት የሰማያዊው ስጦታ አካል ነው። ' ከእምነት የተነሳ መታዘዝ ይሆን ዘንድ'፤ ስለዚህ

ይህን ያሳኩት ሐዋርያት አይደሉም፤ ነገር ግን ጸጋው ቀድሞ መንገዱን ጠረገላቸው። የእነርሱ ድርሻ ዘሮ መስበክ ነበር፤ የማሳመን ሥራው ግን በእነርሱ ውስጥ የሚሠራ የእግዚአብሔር ነበረ። ሉቃስም እንደተናገረው፦ 'ልቧን ከፈተላት' (ሐዋ. ፲፮፥፲፬)፤ ደግሞም የእግዚአብሔርን ቃል ይሰሙ ዘንድ ለተሰጣቸው ይላል።

"ለመታዘዝ" ይላል እንጂ "ለመጠራጠር" ወይም "ለክርክር እና ለድርድር" አይልም። እኛ የተላክነው ለመከራከር ሳይሆን፣ በእጃችን በአደራ የተሰጠንን እንድንሰጥ ነውና። ጌታ የሆነን ነገር ሲናገር፣ የሚሰሙት ሰዎች ስለተነገራቸው ነገር በጥንቃቄ የሚመረምሩና የሚያመነቱ መሆን የለባቸውም፤ ተቀባዮች ብቻ መሆን አለባቸው እንጂ። ሐዋርያት የተላኩት የሰሙትን እንዲናገሩ እንጂ ከራሳቸው ምንም እንዲጨምሩ አይደለምና፤ እኛም በበኩላችን እንድናምን ነው። ምን ብለን እንድናምን? "ስለ ስሙ"። ስለ ባሕርዩ (essence) እንድንመራመር ሳይሆን በስሙ እንድናምን፤ ተአምራትንም የሰራው ይህ ስሙ ነውና። "በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ" ይላልና (ሐዋ. ፫፥፮)። ይህም እምነትን ይጠይቃል፤ እንጂ ማንም እነዚህን ነገሮች በምክንያታዊ ምርምር (reasoning) ሊረዳቸው አይችልም። "'በአሕዛብ ሁሉ መካከል፤ እናንተ ደግሞ ከእነርሱ መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ ናችሁ'" ። እንዴት ? ታዲያ ጳውሎስ ለአሕዛብ ሁሉ ሰበከን ? ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ እልዋሪቆን (Illyricum) ድረስ ያለውን ስፍራ ሁሉ እንደሮጠ፣ ከዚያም አልፎ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ እንደሄደ ለሮሜ ሰዎች ከጻፈው መረዳት ይቻላል። ነገር ግን ወደ ሁሉም ባይደርስ እንኳን፣ የተናገረው ሐሰት አይደለም፤ ምክንያቱም ስለ

ራሱ ብቻ ሳይሆን ስለ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትና ከእነርሱ በኋላ ቃሉን ስለገለጡት ሁሉ ነውና የሚናገረው። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ስለ ራሱ ብቻ ተናግሯል ብንል እንኳ፣ የእርሱን ዝግጁ አእምሮ ስናይና ከሞተ በኋላም እንኳ በዓለም ሁሉ መስበኩን እንደማያቋም ስንረዳ፣ ንግግሩ ምንም ስህተት የለበትም። ስጦታው ምን ያህል ታላቅ እንደሆነና ከቀደመው (ከብሉይ ኪዳን) እጅግ የላቀ መሆኑንም ተመልከት፤ የቀደሙት ነገሮች ለአንድ ብሔር ብቻ ነበሩና፤ ይህ ስጦታ ግን ባሕር እና የብስን ወደ ራሱ ሳበ። ለዚህም ደግሞ ትኩረት ስጥ፤ የጳውሎስ አእምሮ ከሽንገላ ሁሉ እንዴት ነጻ እንደሆነ! በዓለም አናት (ራስ) ላይ እንደተቀመጡ ከሚቆጠሩት ከሮሜ ሰዎች ጋር ሲነጋገር፣ ለእነርሱ ከሌላው የተለየ አላደረገላቸውም እንደ ሌሎቹ አሕዛብ አደረጋቸው እንጂ ፤ እነርሱ በዚያን ጊዜ በሥልጣን ላይ ስላሉና ዓለምን ስለሚገዙ፣ በመንፈሳዊውም ነገር ማንኛውም ዓይነት ብልጫ አላቸው ብሎ አልተናገረም። ነገር ግን የፈለገው፦ 'ለአሕዛብ ሁሉ እንደምንሰብክ ሁሉ፣ ለእናንተም እንሰብካለን' ለማለት ነው፤ ከእስኩቴሶችና (Scythians) ከትራክያውያን (Thracians) ጋር አብሮ በመቁጠር። ይህንን ማሳየት ባይፈልግ ኖሮ "እናንተ ደግሞ ከእነርሱ መካከል" ማለቱ ትርፍ (አላስፈላጊ) በሆነ ነበር። ይህንንም ማድረጉ ትዕቢታቸውን ለመስበር፣ የአእምሯቸውንም ከንቱ ውጥረት ዝቅ ለማድረግና ሌሎችን እንደ ራሳቸው አድርገው እንዲያከብሩ ለማስተማር ነው፤ ስለዚሁ ነጥብ ንግግሩን ይቀጥላል።

ቁጥር ፮፦ "እናንተ ደግሞ ከእነርሱ መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ ናችሁ።"

ይህም ማለት “ከእነርሱ ጋር እናንተም አላችሁ” ማለት ነው፤ እርሱም “ሌሎቹን ከእናንተ ጋር ጠራቸው” አላለም፣ ይልቁንም “እናንተን ከሌሎቹ ጋር” ጠራችሁ አላቸው እንጂ። በክርስቶስ ኢየሱስ ባሪያ ወይም ጨዋ (አርበኛ) የለም ከተባለ፣ ይልቁንም ንጉሥ እና ተራ ሰው (ልዩነት) የለም። ምክንያቱም እናንተም የተጠራችሁ ናችሁ እንጂ በራሳችሁ የመጣችሁ አይደላችሁምና።

ቁጥር ፯፦ "በእግዚአብሔር ለተወደዱና ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ፤ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።"

እንዴት አድርጎ “የተጠራ” የሚለውን ቃል ደጋግሞ እንደሚጠቀም ተመልከት፦ “ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ”፣ “እናንተ ደግሞ የተጠራችሁ”፣ “ለተጠሩት ሁሉ” እያለ። ይህንንም የሚያደርገው ቃል ስለበዛበት ሳይሆን፣ የተደረገላቸውን ውለታ (በረከት) እንዲያስታውሱ ስለፈለገ ነው። ምክንያቱም ካመኑት መካከል እንደ ድሆችና ተራ ሰዎች ሁሉ፣ መኳንንት እና ገዥዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ፣ የደረጃ ልዩነቶችን ወደ ጎን በመተው ለሁሉም በአንድ የጋራ መጠሪያ ይጽፍላቸዋል። ነገር ግን ይበልጥ አስፈላጊ በሆኑትና በመንፈሳዊ ነገሮች ሁሉ ለባሪያዎችም ለጨዋዎችም (ነጻ ለሆኑት) እኩል ተደርገው ከቀረቡ—ለምሳሌ፦ ከእግዚአብሔር የሆነው ፍቅር፣ ጥሪው፣ ወንጌሉ፣ የልጅነት ክብር፣ ጸጋው፣ ሰላሙ፣ መቀደሱና ሌሎች ነገሮች ሁሉ—ታዲያ እግዚአብሔር አንድ ያደረጋቸውንና በታላላቅ ነገሮች የእኩልነት ክብር የሰጣቸውን ሰዎች፣ በምድራዊ ነገር ምክንያት መለየት ከፍጹም ስንፍና በቀር ምን ሊሆን ይችላል? በዚህ ምክንያት፣ ይህ ብፁዕ ሐዋርያ ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ ይህንን ጎጂ ደዌ (ትዕቢትን) አስወግዶ፣ ወደ

በረከቶች ሁሉ እናት ወደ ምትሆን ወደ “ትሕትና”ይመራቸዋል ብዬ አስባለሁ። ይህም ባሪያዎች እውነተኛውን አርነት እስካገኙ ድረስ ከባርነታቸው ምንም ጉዳት እንደማይደርስባቸው ስለሚማሩ የተሻሉ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፤ ጌቶችም የእምነት በረከቶች ቀዳሚውን ስፍራ ካልያዙ በስተቀር ነጻ በመሆናቸው ምንም ብልጫ እንደሌላቸው ስለሚረዱ ገር (ለስላሳ) እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይህንንም ታውቁ ዘንድ ይህንንም ማድረጉ ሁሉንም ነገር በመቀላቀል (በመደባለቅ) ግራ መጋባትን ለመፍጠር ሳይሆን፣ ይልቁንም ከሁሉ የሚበልጠውን ልዩነት ያውቅ ስለነበረ ነው። ለዚህም ነው በሮሜ ላሉት ሁሉ ብሎ ብቻ ዝም ያላለው፤ “በእግዚአብሔር ለተወደዱ” የሚል ትርጉም ያለውን ቃል ጨመረ እንጂ። ይህ ከሁሉ የሚበልጥ መለያ ነው፤ መቀደስ ከየት እንደመጣ ያሳያል። ታዲያ መቀደስ ከየት መጣ ? ከፍቅር መጣ። “ለተወደዱ” ካለ በኋላ “ ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩ “ ማለቱ፣ የበረከቶች ሁሉ ምንጭ ከዚሁ (ከፍቅር) መሆኑን ለማሳየት ነው። “ቅዱሳን” ብሎም አማኞችን ሁሉ ይጠራቸዋል።

“ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።”

ኦ! ስንት ስፍር ቁጥር የሌላቸውን በረከቶች ወደ እኛ የሚያመጣ ሰላምታ! ክርስቶስም ሐዋርያት ወደ ቤቶች ሲገቡ መጀመሪያ እንዲጠቀሙበት ያዘዛቸው ቃል ይህንን ነበር (ሉቃስ ፲÷፭)። ስለዚህ ጳውሎስም በሁሉም ቦታዎች መጀመሪያውን ከጸጋና ከሰላም ያደርጋል፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ያስቆመው ጦርነት ቀላል አልነበረምና፤ ይልቁንም ለረጅም ዘመን የቆየ፣ ልዩ ልዩና ብዙ መልክ ያለው ጦርነት ነበር። ይህም የተገኘው በእኛ ጥረት ሳይሆን በእርሱ ጸጋ ነው። እንግዲህ ፍቅር ጸጋን፣ ጸጋ ደግሞ ሰላምን

ስለሰጠን፣ እርሱም በሰላምታው ውስጥ በተገቢው ቅደም ተከተል አስቀመጣቸው። እነዚህም በረከቶች ለዘላለም ጸንተው እንዲኖሩና እንዳይናወጡ፣ ሌላም ጦርነት ዳግመኛ እንዳይቀሰቀስ ይጸልያል፤ የሰጠውም አምላክ እነዚህን ነገሮች አጽንቶ እንዲጠብቅላቸው ሲለምን እንዲህ ይላል፦ “ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።” በዚህ ጥቅስ ውስጥ 'ከ' (From) የሚለው ቃል ለወልድም ለአብም የጋራ ነው። ይህም “ከእርሱ” ከሚለው ጋር እኩል ነው። ምክንያቱም “ከእግዚአብሔር አብ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል” አላለም፤ ይልቁንም “'ከእግዚአብሔር አባታችንና ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ” አለ እንጂ። ድንቅ ነው! የእግዚአብሔር ፍቅር እንዴት ታላቅ ነው! ጠላቶችና የተዋረድን የነበርን እኛ፣ በአንድ ጊዜ ቅዱሳንና ልጆች ሆንን። “አባት” ብሎ ሲጠራው እነርሱ ልጆች መሆናቸውን ያሳያል፤ “ልጆች” ሲል ደግሞ የበረከቶችን መዝገብ ሁሉ ከፍቶላቸዋል። እንግዲህ ለተሰጠን ስጦታ የሚመጥን አኗኗር እናሳይ፤ በሰላምና በቅድስናም እንጽና። ሌሎች ክብሮች (ምድራዊ ማዕረጎች) ለጊዜው ብቻ ናቸው፤ ከዚህ ሕይወት ጋር አብረው ያበቃሉ፤ በገንዘብም ሊገዙ ይችላሉ (ስለዚህም ማዕረግ ሳይሆኑ የማዕረግ ስሞች ብቻ ናቸው ሊባሉ ይገባል፤ ጉልበታቸውም ባማረ ልብስና በአገልጋዮች መታጀብ ላይ ብቻ ነው)። ከእግዚአብሔር የተሰጠው የመቀደስና የልጅነት ስጦታ ግን በሞት እንኳን አይፈርስም፤ ይልቁንም እዚህም ቢሆን ሰውን ታዋቂ ያደርገዋል፣ ወደፊት ለሚመጣው ሕይወት በምናደርገው ጉዞም አብሮን ይሄዳል። ምክንያቱም በልጅነት ክብር የሚጸናና ቅድስናውን በትጋት የሚጠብቅ ሰው በራሱ ላይ ዘውድ ከደፋና ቀይ ግምጃ (purple) ከለበሰ ንጉሥ ይልቅ እጅግ የበራና ደስተኛ ነው። እንዲህ ያለው ሰው በዚህ

ሕይወት የተትረፈረፈ ሰላም ደስታ አለው፤ በመልካም ተስፋም ያድጋል፤ ለጭንቀትና ለሁከትም ምክንያት የለውም፤ ይልቁንም ዘላቂ ደስታን ያገኛል። ምክንያቱም መንፈሳዊ ጥንካሬና ደስታ የሚገኘው ከታላቅ ሥልጣን፣ ከሀብት መብዛት፣ ከሹመት ክብር፣ ከሰውነት ጥንካሬ፣ ከማዕድ ጣፋጭነት፣ ከልብስ ጌጥነት ወይም ሰዎች ሊደርሱባቸው ከሚችሏቸው ከማናቸውም ምድራዊ ነገሮች አይደለም፤ ነገር ግን ከመንፈሳዊ ስኬትና ከበጎ ሕሊና ብቻ እንጂ። ይህ (ሕሊናው) የጠራለት ሰው፣ ምንም እንኳ የተበጣጠሰ ጨርቅ ቢለብስና በራብ ቢሰቃይም፣ እንዲህ ባለ ቅምጥል ሕይወት ከሚኖሩት ይልቅ የተሻለ መንፈሳዊ ደስታ አለው። እንደዚሁም ክፉ ሥራን እየሠራ መሆኑን የሚያውቅ ሰው፣ የሰውን ሀብት ሁሉ ለራሱ ቢሰበስብ እንኳ፣ እርሱ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪን ነው። በዚህ ምክንያት ጳውሎስ ሁልጊዜ በራብና በዕራቁትነት እየኖረ፣ በየቀኑም እየተገረፈ ሳለ፣ በደስታ ይኖር ነበር፤ በዚያ ዘመን ከነበሩት ነገሥታት (ቄሳሮች) ይልቅ በሰላም ይጓዝ ነበር። አክአብ ግን ንጉሥ ሆኖ ሳለና በቅምጥል ሕይወት ውስጥ እየኖረ፣ ያችን አንዲት ኃጢአት በሰራ ጊዜ (የናቡቴን ወይን ቦታ በወሰደ ጊዜ) ግን ያንጎራጉርና ይተክዝ ነበር፤ ከኃጢአቱ በፊትም ሆነ በኋላ ፊቱ ተለዋውጦ (ጠቁሮ) ነበር። እንግዲህ እውነተኛ ደስታን ማጣጣም ከፈለግን፣ ከሁሉ ነገር በላይ ክፋትን እንሽሽ፣ በጎነትንም እንከተል። ምክንያቱም በንጉሥ ዙፋን ላይ ብንቀመጥ እንኳ፣ ከዚህ ውጭ በሌላ መንገድ ደስታን ማግኘት በተፈጥሮ የማይቻል ነውና። ለዚህም ነው ጳውሎስ፦ “የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም ነው” (ገላ. ፭፥፳፪) የሚለው። እንግዲህ እዚህ በምድር ላይ የደስታ ባለቤት እንድንሆን፣ ወደፊትም የሚመጣውን መንግሥት እንድንወርስ፣ ይህ ፍሬ በእኛ ዘንድ እንዲያድግ እናድርግ።

ይህም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰው ወዳድነት ይሁንልን፤ በእርሱና ከእርሱ ጋር ለአብ ለመንፈስ ቅዱስም ክብር ይሁን፤ ዛሬም ዘወትርም እስከ ዘላለሙ ድረስ አሜን ።

# ድርሳን ሁለት ( homily II )

ሮሜ ፩፥፰፦ "ስለ ሁላችሁ እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች አስቀድሜ በአምላኬ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩልእመሰግናለሁ።"

ይህ መግቢያ ለዚህ ብፁዕ መንፈስ (ለጳውሎስ) የሚመጥን ነው፤ ለሰው ልጆችም ሁሉ ከመልካም ሥራዎቻቸውና ከንግግራቸው መጀመሪያውን ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡ የሚያስተምር ነው። እንዲሁም ስለ ራሳቸው መልካም ነገር ብቻ ሳይሆን ስለ ሌሎችም ስኬት ምስጋና ማቅረብን ያስተምራል። ይህም ነፍስን ከቅናትና ከክፉ ምኞት ያጠራል፤ እግዚአብሔርንም እንዲህ ምስጋና ወደሚያቀርብ አፍቃሪ መንፈስ ይበልጥ ይስበዋል። ለዚህም ነው በሌላ ስፍራ፦ "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት

ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ" (ኤፌ. ፩፥፫) የሚለው።

ባለጠጋ ስንሆን ብቻ ሳይሆን ድሃ ስንሆንም ምስጋና ማቅረብ ይገባናል፤ ጤነኞች ስንሆን ብቻ ሳይሆን ስንታመምም፣ ነገሮች ሲሳኩ ብቻ ሳይሆን መከራ ሲገጥመንም እንዲሁ። ምክንያቱም ጉዳዮቻችን በመልካም ነፋስ (በሰላም) ሲጓዙ አመስጋኝ መሆን የሚደነቅ አይደለም። ነገር ግን ታላቅ ማዕበል ሲነሳብን፣ መርከቧም ስትወዛወዝና አደጋ ላይ ስትሆን፣ ያን ጊዜ ትዕግሥትንና የበጎ ልብ ባለቤትነትን ለማሳየት ታላቁ ጊዜ ነው። በዚህ ምክንያት ኢዮብ ከዚያ (ከመከራው) አክሊልን አገኘ፤ የሰይጣንንም ክፉ አፍ ዘጋ፤ በደስታ ዘመኑም አመስጋኝ የነበረው በሀብቱ ምክንያት ሳይሆን ለእግዚአብሔር ካለው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ መሆኑን በግልጽ አሳየ። ደግሞም (ጳውሎስ) ለምን ዓይነት ነገሮች ምስጋና እንደሚያቀርብ ተመልከት፦ እንደ ሥልጣንና ክብር ስላሉ ምድራዊና ጠፊ ነገሮች አይደለም (እነዚህ ነገሮች ምንም ግምት የማይሰጣቸው ናቸውና)፤ ነገር ግን ስለ እውነተኛ በረከቶች—ስለ እምነትና ስለ ንግግር ድፍረት  ነው እንጂ። ምስጋናውንም እንዴት ባለ ጥልቅ ስሜት እንደሚያቀርብ ተመልከት፤ "ለእግዚአብሔር" ሳይሆን "ለአምላኬ" ነው የሚለው። ነቢያትም ለሁሉም የጋራ የሆነውን (አምላክን) የራሳቸው በማድረግ እንዲህ ይላሉ። ነቢያት እንዲህ ማድረጋቸው ምን ይደንቃል? እግዚአብሔር ራሱ ራሱን የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ብሎ በመጥራት የእነርሱ ብቻ እንደሆነ አድርጎ በግልጽ ይናገራልና።   "እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች" ታዲያ ዓለም ሁሉ የሮሜ ሰዎችን እምነት ሰምቶ ነበርን? አዎን፤ በእርሱ አባባል ዓለም ሁሉ ሰምቷል። (ወይም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ

ለዓለም ሁሉ ተሰምቷል)። ይህም የማይመስል ነገር አይደለም።
ምክንያቱም ከተማዋ (ሮም) የማይታወቅ ስፍራ ሳትሆን፣ ከፍታ
ላይ እንዳለች (እናት እንደመሆኗ) በሁሉም ረገድ ጎልታ የምትታይ
ነበረች። ነገር ግን የስብከቱን ኃይል ተመልከት ብዬ እለምንሃለሁ፤
በአጭር ጊዜ ውስጥ በቀራጮችና በዓሣ አጥማጆች አማካኝነት
የከተሞች ሁሉ ራስ የሆነችውን ከተማ እንዴት እንደያዘች!
ሐዋርያቱ የሮሜ ሰዎች መምህራንና መሪዎች ሆኑ። እንግዲህ
በእነርሱ ዘንድ ሁለት ታላላቅ በጎነቶችን መሰከረ፤ ይኸውም
ማመናቸውንና ያመኑትም በድፍረት (በመገለጥ) መሆኑን ነው፤
ይህም ዝናቸው በዓለም ሁሉ እስኪሰማ ድረስ ታላቅ ነበረ።
'እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች' ይላል እንጂ፤ የቃል
ክርክራችሁ ወይም ምርምራችሁ ወይም የፍልስፍና ድርደራችሁ
አላለም። ሆኖም ግን ለትምህርቱ (ለስብከቱ) ብዙ መሰናክሎች
ነበሩ። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ የዓለምን ግዛት በቅርቡ
ተቆጣጥረው ስለነበር በትዕቢት ተወጥረው ነበር፤ በሀብትና
በቅምጥል ሕይወትም ይኖሩ ነበር። ስብከቱን ይዘው የመጡት
ደግሞ ዓሣ አጥማጆች ነበሩ፤ እነርሱም አይሁድ ሲሆኑ፣ አይሁድ
ደግሞ በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠሉና የተናቁ ሕዝቦች ነበሩ።
የሚሰግዱለትም በይሁዳ ያደገውንና “የተሰቀለውን” (ክርስቶስን)
እንዲሆን ታዘዙ። ከትምህርቱም ጋር መምህራኑ በቅምጥል
ሕይወት ለለመዱና በምድራዊ ነገር ለሚታወቁ ሰዎች፣ እጅግ
ጥብቅ (ቁጥብ) የሆነን አኗኗር ሰበኩ። ሰባኪዎቹም ድሆች፣ ተራ
ሰዎች፣ ከማይታወቅ ቤተሰብ የተገኙና በማይታወቁ ሰዎች
የተወለዱ ነበሩ። ነገር ግን ከእነዚህ ነገሮች መካከል አንዳቸውም
የቃሉን ጉዞ አላገዱትም። የተሰቀለው (የክርስቶስ) ኃይል ቃሉን
በየቦታው ለማድረስ እጅግ ታላቅ ነበረና።

“ተሰምቷል” ይላል፤ “ታይቷል” አይልም፣ ነገር ግን ሰው ሁሉ በአፉ ስለ እነርሱ እንደሚናገር ለማመልከት “ተሰምቷል” አለ። በእርግጥ ይህንን ምስክርነት ለተሰሎንቄ ሰዎች ሲሰጥ ሌላ ነገር ጨምሮ ነበር። “ከእናንተ ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል ወጥቷልና” ካለ በኋላ “ምንም እንድንናገር አያስፈልገንም” ሲል ጨምሮአል (፩ ተሰ. ፩፥፰)። ምክንያቱም ደቀ መዛሙርቱ በመምህራኑ ቦታ ተተክተው ነበርና፤ በንግግር ድፍረታቸው ሁሉንም እያስተማሩና ወደ ራሳቸው እየሳቡ። ስብከቱ በማንኛውም ስፍራ አልቆመም፤ ይልቁንም ከእሳት ይልቅ በፍጥነት በዓለም ሁሉ ተሰራጨ። እዚህ ላይ ግን 'ተሰምቷል' የሚለውን ብቻ ተጠቀመ። 'ተሰምቷል' ማለቱም መልካም ነው፤ ከተነገረው ላይ ምንም መጨመር ወይም መቀነስ እንደማያስፈልግ ያሳያልና። የመልዕክተኛ ሥራ የተነገረውን ብቻ ከአንዱ ወደ ሌላው ማድረስ ነውና። በዚህ ምክንያት ካህኑ “መልዕክተኛ” ይባላል (ሚል.፪፥፯)፤ የራሱን ቃል ሳይሆን የላከውን ቃል ስለሚናገር። ሆኖም ግን ጴጥሮስ በዚያ ሰብኮ ነበር። (ጳውሎስ) ግን የእርሱን(የጴጥሮስን) ሥራ እንደ ራሱ አድርጎ ይቆጥረዋል። ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት፣ እርሱ በምን ያህል ደረጃ ከቅናት የራቀ ነበረ!

## ቁጥር ፱፦ "በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና።"

እነዚህ የአንድ ሐዋርያ የልብ አፍቃሪነት ቃላት ናቸው፤ የአባትነት አሳቢነት መግለጫዎች ናቸው! ለመሆኑ ምንድን ነው የሚለው? ለምንስ እግዚአብሔርን ምስክር አድርጎ ይጠራል? ለእነርሱ ያለውን ስሜት መግለጥ ነበረበት። እስከዚያ ጊዜ ድረስ በአካል

አይቷቸው ስለማያውቅ፣ ሰውን ምስክር ከማድረግ ይልቅ ልብን የሚመረምረውን (እግዚአብሔርን) ምስክር አድርጎ ጠራ።

እርሱ "እወዳችኋለሁ" እያለ ስለነበረ፣ ለዚህም ምልክት ይሆን ዘንድ ስለ እነርሱ ሳያቋርጥ መጸለዩንና ወደ እነርሱ ለመምጣት መመኘቱን ስለጠቀሰ፣ ይህም (በአካል ስላልታዩ) በራሱ ግልጽ ስላልነበረ፣ ወደ ታማኙ ምስክር (ወደ እግዚአብሔር) ራሱን ያስጠጋል። ለመሆኑ ከእናንተ መካከል በቤቱ ሲጸልይ መላዋን ቤተክርስቲያን እንደሚያስታውስ ሊመካ የሚችል ይኖር ይሆን? እኔ ግን አይመስለኝም። ጳውሎስ ግን ስለ አንዲት ከተማ ብቻ ሳይሆን ስለ ዓለም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ይቀርብ ነበር፤ ይህም አንድ ጊዜ፣ ሁለት ጊዜ ወይም ሦስት ጊዜ ሳይሆን 'ሳያቋርጥ' ነበር። ማንንም ቢሆን በሐሳብ ማሰብ ያለ ጥልቅ ፍቅር የማይሆን ከሆነ፣ በጸሎት ውስጥ መያዝ ያውም ዘወትር መያዝ ምን ያህል ታላቅ ፍቅርና ወዳጅነትን እንደሚጠይቅ አስቡት።

"በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው" ፦ሲልም፣ በአንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ጸጋና የራሱን ትሕትና ያሳየናል። የእግዚአብሔር ጸጋ የተገለጠው እንዲህ ያለውን ታላቅ ጉዳይ (አደራ) ስለሰጠው ነው፤ የራሱ ትሕትና ደግሞ ይህንን ሁሉ ለራሱ ትጋት ሳይሆን ለመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት በመስጠቱ ነው። "ወንጌል"የሚለውን መጨመሩ ደግሞ የአገልግሎቱን ዓይነት ያሳያል። የአገልግሎት ዓይነቶች ብዙና የተለያዩ ናቸውና። በነገሥታት ሥር ሁሉም በአንድ የንጉሥ ሥልጣን ሥር ቢሆኑም፣ ሁሉም ግን በአንድ ነገር ላይ አያገለግሉም፤ ለአንዱ የሠራዊት መሪነት፣ ለሌላው የከተሞች አስተዳዳሪነት፣ ለሌላው ደግሞ የቤተ መዛግብት ጠባቂነት እንደሚሰጠው ሁሉ፤ በመንፈሳዊ ነገሮችም እንዲሁ ነው። አንዱ እግዚአብሔርን የሚያገለግለውና የሚደክመው

በማመንና የራሱን ሕይወት በማስተካከል ነው፤ ሌላው እንግዶችን በመቀበል፣ ሌላው ደግሞ ችግር ያለባቸውን በመርዳት ነው።

በሐዋርያት ዘመንም እንደነ እስጢፋኖስ ያሉት መበለቶችን በመንከባከብ እግዚአብሔርን ያገለግሉ ነበር፤ ሌሎች ደግሞ ቃሉን በማስተማር ያገለግሉ ነበር፤ ከእነዚህም መካከል ጳውሎስ ወንጌልን በመስበክ የሚያገለግል ነበረ። የአገልግሎቱም መልክ እንዲህ ነበረ፤ የተሾመው ለዚህ ነበርና። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔርን ምስክር አድርጎ መጥራት ብቻ ሳይሆን፣ የተሰጠውን አደራ ጭምር ይናገራል። ይህም እንዲህ ያለ ታላቅ ነገር በእጁ ላይ እያለ፣ ይህን አደራ የሰጠውን አምላክ በሐሰት ምስክርነት እንደማይጠራ ለማሳየት ነው። በዚህም ሌላ ነጥብ ሊያሳይ ፈልጓል፤ ይኸውም ለእነርሱ ይህ ፍቅርና አሳቢነት ሊኖረው የግድ እንደሆነ ነው። 'እንዲህ ላለች ታላቅና ንጉሣዊት ከተማ የምጨነቅ እኔ ማን ነኝ? ከየትስ መጣሁ?' እንዳይሉ፤ የተሰጠው አገልግሎት ወንጌልን ማወጅ እስከሆነ ድረስ ይህ አሳቢነት ሊኖረው እንደሚገባ ያሳያል። ይህ አደራ በእጁ ያለበት ሰው፣ ቃሉን የሚቀበሉትን ሰዎች ሁልጊዜ በሐሳቡ ሊይዛቸው ይገባልና። በተጨማሪም 'በመንፈሴ' በማለቱ ይህ አገልግሎት ከአረማውያንም ሆነ ከአይሁድ (ሥርዓት) እጅግ የላቀ መሆኑን ያሳያል። ምክንያቱም የአረማውያን አገልግሎት ሥጋዊም ስህተትም ያለበት ነው፤ የአይሁድ አገልግሎት ደግሞ እውነተኛ ቢሆንም እርሱም ቢሆን ሥጋዊ ነው። የቤተክርስቲያን አገልግሎት ግን ከአረማውያን ተቃራኒ ሲሆን፣ ከአይሁድ ደግሞ በብዙ እጥፍ የላቀ ነው። ምክንያቱም የእኛ የአገልግሎት መልክ በበጎች፣ በበሬዎች፣ በጢስና በስብ ሳይሆን፣ በመንፈሳዊት ነፍስ ነውና። ይህም ክርስቶስ፦ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም

በመንፈስናበእውነት ሊሰግዱለት ይገባቸዋል" (ዮሐ. ፬፥፳፬) በማለት የገለጠው ነው "በልጁ ወንጌል" ከላይ "የአብ ወንጌል" ብሎት ነበር፤ እዚህ ላይ ደግሞ "የወልድ" (የልጁ) ይለዋል። የአብ ወይም የወልድ ብሎ መጥራት ልዩነት የለውምና! ምክንያቱም የአብ የሆነው ሁሉ የወልድ፣ የወልድ የሆነውም ሁሉ የአብ መሆኑን ካለችው ከዚያች ከብጽዕት ድምፅ (ከክርስቶስ ቃል) ተምሯልና፦"የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው፥ የአንተም የእኔ ነው" (ዮሐ. ፲፯፥፲) እንዳለ "ሁልጊዜ በጸሎቴ ስለ እናንተ ሳላቋርጥአሳስባለሁ" ይህ የእውነተኛ ፍቅር ድርሻ ነው። እዚህ ላይ አንድ ነገር ብቻ የተናገረ ቢመስልም፣ አራት ነገሮችን ግን ገልጧል፦ ያስባቸው እንደነበር፣ ይህንንም ሳያቋርጥ ያደርግ እንደነበር፣ በጸሎቱ ውስጥ መሆኑንና ለእነርሱም ታላላቅ ነገሮችን እንደሚለምንላቸው ነው።

ቁጥር ፲-፲፩፦ "ወደ እናንተ ለመምጣት ምናልባት በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገዴን እንዲያቀናልኝ ሁልጊዜ እለምናለሁ።"

እነርሱን ለማየት እንዴት እጅግ እንደሚናፍቅ ተመልከት፤ ሆኖም ግን በእግዚአብሔር ፊት መልካም መስሎ ካልታየ በቀር እነርሱን ለማየት አይፈልግም። ናፍቆቱ ከእግዚአብሔር ፍርሃት ጋር የተደባለቀ ነውና። ይወዳቸዋል፣ ወደ እነርሱ ለመምጣትም ይቸኩላል፤ ሆኖም ስለወዳቸው ብቻ እግዚአብሔር ከፈቀደው ውጭ እነርሱን ማየት አይሻም። እውነተኛ ፍቅር ይህ ነው፤ እኛ ግን በሁለቱም በኩል የፍቅርን ሕግ ጥሰን የምንሳሳት ነን። ወይ ማንም አንወድም፣ ካፈቀርንም ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት መልካም ካልሆነው ነገር ጋር እንወድዳለን፤ በሁለቱም መንገድ መለኮታዊውን ሕግ እንጥሳለን። እነዚህ ነገሮች ሲነገሩ የሚከብዱ

ከሆኑ፣ ሲደረጉማ ይበልጥ ይከብዳሉ 'እንዴትስ ነው እግዚአብሔር ከሚወደው ውጭ የምንወደው?' ትል ይሆናል። ክርስቶስ በራብ ሲሰቃይ (ድሆችን ማለቱ ነው) ችላ ብለን፣ ለልጆቻችን፣ ለጓደኞቻችንና ለዘመዶቻችን ከሚያስፈልጋቸው በላይ ስናቀርብላቸው ነው። ይልቁንም ጉዳዩን ከዚህ በላይ መውሰድ ምን ያስፈልጋል? ማንኛውም ሰው የገዛ ሕሊናውን ቢመረምር፣ ይህ በብዙ ነገሮች ውስጥ እንደሚከሰት ያገኘዋል ይህ ብፁዕ ሰው (ጳውሎስ) ግን እንደዚያ አልነበረም። እርሱ እንዴት መውደድ እንዳለበትና በተገቢው መንገድ መውደድን ያውቅ ነበር። ሰዎችን በመውደድ ከሁሉ ቢበልጥም፣ የፍቅርን ልክ ግን አላለፈም። እንግዲህ በእርሱ ውስጥ ሁለት ነገሮች እጅግ በርትተው ይታያሉ፦ እግዚአብሔርን መፍራትና ለሮሜ ሰዎች ያለው ናፍቆት። ምክንያቱም ሁልጊዜ መጸለይ፣ ባልተሰጠውም ጊዜ ተስፋ አለመቁረጥ እጅግ ታላቅ ፍቅርን ያሳያል። እየወደዱ ግን እንዲህ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት ደግሞ ጥልቅ የሆነ አክብሮትን ያሳያል። በሌላ ስፍራ ግን “ሦስት ጊዜ ጌታን የለመነ” (፪ ቆሮ. ፲፪፥፰) ቢሆንም፣ አልተሰጠውም ብቻ ሳይሆን፤ በተቃራኒው ልመናው ተቀባይነት ባላገኘ ጊዜ ስላልተሰማ እጅግ አመስጋኝ ነበር። ስለዚህ በሁሉም ነገሮች ወደ እግዚአብሔር ይመለከት ነበር። እዚህ ጋር ግን (ወደ ሮሜ የመሄዱን ፈቃድ) አግኝቷል፤ ሆኖም ያገኘው በጠየቀበት ጊዜ ሳይሆን ዘግይቶ ነው፤ በዚህም ቢሆን አላጉረመረመም። እነዚህንም ነገሮች የምጠቅሰው፣ ጸሎታችን ባልተሰማ ጊዜ ወይም መልሱ በዘገየ ጊዜ እንዳናዝን ነው። ምክንያቱም ለሁለቱም (ለተሰማውም ላልተሰማውም ጸሎት) ምስጋናውን ካቀረበውና ለዚህም በቂ ምክንያት ካለው ከጳውሎስ አንበልጥምና። አንዴ ራሱን ሁሉን ለሚገዛው (ለእግዚአብሔር) እጅ አሳልፎ ከሰጠ በኋላ፣ ጭቃ ለሸክላ ሠሪ

እንደሚገዛ እርሱም ለዚያ ተገዝቶ እግዚአብሔር ወደመራው ስፍራ ሁሉ ይከተል ነበር። እነርሱን ለማየት እንደሚናፍቅ ከተናገረ በኋላ፣ የናፍቆቱን ምክንያት ጠቀሰ፤ እርሱም ምንድን ነው ?

## ቁጥር ፲፩፦ "ትጸኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ ላያችሁ እናፍቃለሁና።"

ምክንያቱም እርሱ እንደ ብዙዎቹ አሁን እንደሚጓዙት ያለ አንዳች አስፈላጊና ጠቃሚ ዓላማ አልነበረም የሚጓዘው፤ ነገር ግን ለአስፈላጊና እጅግ አንገብጋቢ ለሆኑ ጉዳዮች ነበር። ሐሳቡንም በግልጽ አልነገራቸውም፣ ነገር ግን በምልክት (በጥቆማ) ነው የገለጸው፤ “እንዳስተምራችሁ”፣ “እንድመክራችሁ” ወይም “የጎደለውን ልሞላላችሁ”አላለም፤ ነገር ግን “እንዳካፍላችሁ” አለ እንጂ። ይህም የሚሰጣቸው ነገር የራሱ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን የተቀበለውን እንደሚያካፍላቸው ለማሳየት ነው። እዚህ ጋርም ቢሆን “አንዳንድ” በማለት ትሑት ይሆናል፤ ይህም ማለት “ትንሽ” እና “ከእኔ አቅም ጋር የሚመጥን” ማለቱ ነው። ታዲያ  አሁን ልታካፍለን የምትችለው ይህች “ትንሽ” ነገር ምንድን ናት? እርሷም፦ “ትጸኑ ዘንድ” (እንዲያጸናችሁ) የሚለው ነው።

እንግዲህ አለመንሸራተትና በጽናት መቆምም ቢሆን ከጸጋ የሚገኝ ነው። ነገር ግን ስለ ጸጋ ስትሰሙ፣ በእኛ በኩል ያለው የውሳኔ (የተጋድሎ) ዋጋ ቀርቷል ብላችሁ እንዳታስቡ። እርሱ ስለ ጸጋ የተናገረው የእኛን የተጋድሎ ድካም ዝቅ ለማድረግ ሳይሆን፣ በትዕቢት የተወጠረን መንፈስ ዝቅ ለማድረግ ነው።  ስለዚህ ጳውሎስ ይህንን 'የጸጋ ስጦታ' ስላለው ብቻ አንተ ዘና አትበል። እርሱ በታላቅ ቅንነቱ መልካም ሥራዎችን እንኳን 'ጸጋዎች' ብሎ መጥራት ያውቅበታልና፤ ምክንያቱም በእነዚህም ቢሆን ከላይ

የሚመጣ ታላቅ ረዳትነት ያስፈልገናል። ነገር ግን "'ትጸኑ ዘንድ" በማለቱ፣ ብዙ ማስተካከያ እንደሚያስፈልጋቸው በስውር ያሳያል፤ ሊላቸው የፈለገው እንዲህ ነውና፦ "ሌላ ምክንያት ኖሮኝ ሳይሆን፣ እናንተን በሚገባ ለማጽናት፣ ለማበርታትና ለመትከል ለረጅም ጊዜ እናንተን ለማየት ተመኝቼም ጸልዬም ነበር ። በእግዚአብሔር ቃል ትጸኑ ዘንድ፤ ይኸውም ሁልጊዜ የምትወዛወዙ እንዳትሆኑ ነው። ነገር ግን እርሱ (ጳውሎስ) ይህንን በቀጥታ አልተናገረም (ምክንያቱም ይህ ሊያስደነግጣቸው እንደሚችል ያውቃልና)፤ ይልቁንም በሌላ መንገድ በለዘበ ድምፅ ያንኑ ነጥብ ይጠቁማቸዋል። "ትጸኑ ዘንድ" በሚለው ቃል ይህንን ግልጽ አድርጎታል። ከዚያም ይህ አባባል (በአንባቢው ዘንድ) አስቸጋሪ ሊሆን ስለሚችል፣ ቀጥሎ በሚመጣው ሐሳብ እንዴት እንደሚያለሰልሰው ተመልከት። "እኛ የምንወዛወዝ ነን? የምንገላበጥስ ነን? ለመጽናት ያንተ ንግግር ያስፈልገናልን?" እንዳይሉ፤ ማንኛውንም ዓይነት ተቃውሞ ቀድሞ በመገመት እንዲህ በማለት ያስወግደዋል።

ቁጥር ፲፪፦ "ይኸውም በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን በእናንተ ዘንድ እንድንጽናና ነው።"

እንዲህ ማለቱ ነው፦ "እናንተን ለመውቀስ የተናገርኩ እንዳይመስላችሁ። እንዲህ ያልኩት በዚህ ስሜት አይደለም። ታዲያ ልል የፈለግሁት ምንድን ነው? እናንተ በየአቅጣጫው (በሚያሳድዷችሁ ሰዎች) እየተገፋችሁና ብዙ መከራዎችን እየተቀበላችሁ ነው። ስለዚህ እናንተን እንዳጽናናችሁ፣ ወይም ደግሞ እናንተን ብቻ እንዳጽናና ሳይሆን እኔም ራሴ መጽናናትን ከእናንተ ዘንድ እንድቀበል እናፍቃለሁ።"

የመምህሩን ጥበብ ተመልከት! “'ልታጸኑ ዘንድ” (እንዲያበረታችሁ) አለ፤ ይህ አባባል ለደቀ መዛሙርቱ ከባድና የሚያስቆጭ ሊሆን እንደሚችል አወቀ። ስለዚህ “እንድንጽናና” አለ። ይህ ግን አሁንም ቢሆን ምንም እንኳ እንደ ቀድሞው ባይሆንም አሁንም ከባድ ነው። ስለዚህ በዚህም ውስጥ የሚከፋውን ነገር በመቀነስ፣ ንግግሩን በሁሉም በኩል በማለስለስና በቀላሉ ተቀባይ እንዲሆን ያደርገዋል። ምክንያቱም “እንድንጽናና” ብሎ ብቻ አልተናገረም፤ ነገር ግን “ከእናንተ ጋር አብረን እንድንጽናና” አለ እንጂ። በዚህም ብቻ አልረካም፤ ነገር ግን “በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት” በማለት ይበልጥ የሚያለሰልስ ቃል ጨመረ። ኦ! ትሕትናው ምንኛ ታላቅ ነው! እነርሱ በእርሱ እንደሚፈልጉት ሁሉ፣ እርሱም በእነርሱ እንደሚፈልግ አሳየ። ደቀ መዛሙርቱንም በመምህራን ቦታ ላይ አስቀመጣቸው፤ በእርሱ በኩል ምንም ዓይነት ብልጫ እንዲቀር አላደረገም፣ ነገር ግን ፍጹም እኩልነታቸውን አመለከተ። “ጥቅሙ የሁለታችንም ነው፤ እኔ ከእናንተ መጽናናትን እፈልጋለሁ፣ እናንተም ከእኔ” ማለቱ ነው። ይህም እንዴት ሊሆን ይችላል? “በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት።” ምክንያቱም ልክ እንደ እሳት፣ አንድ ሰው ብዙ መብራቶችን (ብርሃኖችን) በአንድ ላይ ቢሰበስብ ታላቅ ነበልባል እንደሚቀጣጠል ሁሉ፤ በምዕመናንም ዘንድ በተፈጥሮ የሚሆነው ይህ ነው። ከሌሎች ተነጥለን በራሳችን ስንሆን መንፈሳችን ይረበሻል (መንፈሳዊ ኃይላችን ይቀንሳል)። ነገር ግን አንዳችን ሌላችንን ስናይና ከራሳችን አባላት ጋር ስንተሳሰር የምንቀበለው መጽናኛ ታላቅ ነው። አሁን ባለንበት ጊዜ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ በከተማም ይሁን በበረሃ ውስጥ (ብዙ አማኞች ባሉበት) እና ክህደት ሁሉ በጠፋበት ዘመን ያለነውን ሁኔታ አትመልከት፤ ነገር ግን በዚያን ጊዜ ደቀ

መዛሙርት መምህራቸውን ማየታቸው፣ ከሌላ ከተማ የመጡ ወንድሞችም ከወንድሞቻቸው ጋር መገናኘታቸው ምንኛ ታላቅ በጎ ነገር እንደነበረ አስብ።

የምለውንም ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ አንድ ምሳሌ ላምጣ፦ (ፈጽሞ አይሁንና!) ምናልባት ወደ ፋርስ ወይም ወደ ስኩቴስ (Scythians) ወይም ወደ ሌላ አረማዊ አገር ተማርከን ብንወሰድ፣ በየከተሞቻቸውም ሁለት ሁለት ወይም ሦስት ሦስት ሆነን ብንበታተን፤ ከዚያም በድንገት ከዚህ (ከአገራችን) የሆነ ሰው ወደ እኛ ቢመጣ የምናገኘውን የመጽናናት ምርት እስኪ አስቡት! በወኅኒ ያሉትንስ አታዩአቸውም? የሚያውቁትን ሰው ካዩ እንዴት እንደሚነቃቁና በደስታም እንደሚረበሹ ? የዚያን ዘመን ሁኔታ ከምርኮና ከወኅኒ ጋር ብናነጻጽረው ምንም አይደንቅ። ምክንያቱም እነርሱ ተበታትነው፣ እየተገፉ፣ በራብና በጦርነት መካከል እየኖሩ፣ በየቀኑም ሞትን በፍርሃት እየጠበቁ፣ ጓደኞቻቸውንና ዘመዶቻቸውን እንኳን እየጠረጠሩ፣ በዚህ ዓለም እንደ ባዕድ አገር ይኖሩ ስለነበር ከእስረኞች ይልቅ እጅግ የከፋ መከራን ይቀበሉ ነበር። ለዚህ ነው ልታጸኑ ዘንድና በእኛ ዘንድ በጋራ እምነታችን እንድንጽናና" ያለው።

ይህንንም ያለው እርሱ ከእነርሱ እርዳታ ፈልጎ አይደለም (ይህማ ከቶ እንዴት ይሆናል? እንደ ብረትና እንደ ዐለት የጠነከረው፣ እንደ መንፈሳዊ አልማዝ የሆነውና የቆጠራቸው ከተሞች ኃላፊነት የሚመጥነው የቤተክርስቲያን ምሰሶ እርዳታ ይፈልጋልን ?)፤ ነገር ግን አነጋገሩ ኃይለኛና ወቀሳውም የበረታ እንዳይሆንበት ነው እንጂ። ሆኖም "መጽናናቱ" በእነርሱ እምነት ማደግ ያገኘው ደስታ ነው፣ ጳውሎስም ይህንን ይፈልግ ነበር ቢባል አሁንም ትርጉሙ ስህተት አይሆንም። "ታዲያ የምትመኝ፣ የምትጸልይ፣ በዚህም

መጽናናትን የምታገኝና የምትሰጥ ከሆነ፤ ለመምጣት ምን ያግድሃል ?" የሚል ጥያቄ ቢነሳ፤ ይህን ጥርጣሬ ለማስወገድ እንዲህ ይላል፦

ቁጥር ፲፫፦ "ወንድሞች ሆይ፥በሌሎች አሕዛብ ደግሞ እንደሆነ በእናንተም ፍሬ አገኝ ዘንድ ወደ እናንተ ልመጣ ብዙ ጊዜ እንደ አሰብሁ እስከ አሁን ግን እንደ ተከለከልሁ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።"

እዚህ ጋር እንደ ባሪያ የሆነ ታላቅ መታዘዝንና ድንቅ የሆነ በጎ ጠባይ እናያለን! "ተከልክያለሁ" አለ እንጂ፤ ለምን

እንደተከለከለ ግን ለመናገር አልሞከረም። የጌታውን ትዕዛዝ አይመረምርም፣ ይታዘዛል እንጂ። አንድ ሰው "ዓለም ሁሉ የሚያያትና እንዲህ ያለች ታላቅ ከተማ ወደ ክርስቶስ እንድትመለስ እግዚአብሔር ለምን ከለከለ ?" ብሎ ጥያቄ ሊያነሳ ይችል ይሆናል እንዲህ ያለችውን ዓለምን የምትገዛ ከተማን ማሸነፍ ከተቻለ፣ በእርሷ ሥር ያሉትን አገራት መማረክ ቀላል በሆነ ነበር።

ዋናዋንና ንጉሣዊቷን ከተማ ትቶ በዙሪያዋ ባሉ ጥገኞች ላይ መቆየት ደግሞ ዋናውን ነጥብ እንደመዘንጋት ይቆጠራል። ነገር ግን ጳውሎስ በእነዚህ ነገሮች ውስጥ ራሱን አላስጨነቀም፤ ይልቁንም ለማይመረመረው መለኮታዊ ጥበብ ራሱን አስገዛ። በዚህም የነፍሱን ትክክለኛ ባሕርይ አሳየ፤ እኛንም የሚደረገው ነገር የብዙዎችን አእምሮ የሚረብሽ ቢመስል እንኳን፣ እግዚአብሔርን ፈጽሞ እንዳንጠይቀው አስተማረን። የጌታ ድርሻ ማዘዝ ብቻ ሲሆን፣ የባሪያ ድርሻ ደግሞ መታዘዝ ነውና። ለዚህ ነው "ተከልክያለሁ" አለ እንጂ ለምን እንደሆነ ያልተናገረው፤ "እኔ

ራሴ እንኳን አላውቀውም፤ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ምክር ወይም ሐሳብ ከእኔ አትጠይቁ" ማለቱ ነው። "ሥራ ለሠራተኛው፦ ስለ ምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ? ሊለው ይችላልን ?" (ሮሜ ፱፥፳)**። ለመሆኑ ለምን ለማወቅ ትፈልጋለህ ? ሁሉም ነገር በእርሱ ጥበቃ ሥር እንደሆነ፣ እርሱ ጥበበኛ እንደሆነና ምንም ነገር ያለ ዓላማ እንደማያደርግ አታውቅምን ? እርሱ ከወለዱህ በላይ እንደሚወድህ፣ ከአባት አሳቢነትና ከእናት ጭንቀት በላይ ለአንተ እንደሚራራልህስ አታውቅምን ? እንግዲህ ከዚህ በላይ አትፈልግ፣ አንድ እርምጃም አትራመድ፤ ምክንያቱም ይህ (እግዚአብሔር ያውቃል ማለት) ላንተ በቂ መጽናኛ ነውና። በዚያን ጊዜም ቢሆን ለሮሜ ሰዎች የተደረገው ነገር በሚገባ የታቀደ ነበረ። አሠራሩን ባታውቀው እንኳን አትጨነቅ፤ ምክንያቱም የእምነት ዋናው መገለጫ የአምላክን አሠራር ምስጢር ባታውቀውም እንኳ የእርሱን ጥበብ በትሕትና መቀበል ነውና ። ጳውሎስ ትኩረት በሰጠበት ነገር ላይ ከተሳካለት በኋላ (ይኸውም፦ ወደ እነርሱ ያልመጣው እነርሱን ንቆ ሳይሆን፣ እጅግ እየፈለገ ቢከለከል መሆኑን ካስረዳ በኋላ) እና ከቸልተኝነት ክስ ራሱን ካነጻ በኋላ፣ እነርሱን ለማየት ያለው ጉጉት ከእነርሱ ያላነሰ መሆኑን አሳመናቸው ። በተጨማሪም ፍቅሩን በሌሎች ነገሮች ገለጠ። "ተከልክዬ በነበረበት ጊዜም ቢሆን ጥረቴን አላቆምኩም ነበር፤ ሁልጊዜ እሞክር ነበር፣ ሁልጊዜም እከለከል ነበር፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ሳልጣላ ፍቅሬን እንደያዝኩ ጸናሁ" ማለቱ ነው። ሐሳቡን በልቡ በመያዙና ጥረቱን ባለማቋረጡ ፍቅሩን አሳየ፤ በመከልከሉም ጊዜ ባለመታገሉ (ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመገዛቱ) ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር አሳየ።

## "በእናንተ ደግሞ እንደ ሌሎች አሕዛብ ጥቂት ፍሬ አገኝ ዘንድ..."

የናፍቆቱን ምክንያት አስቀድሞ ነግሯቸው ነበር፤ ይህም ለሐዋርያነቱ የሚገባ መሆኑን አሳይቷል። ሆኖም እዚህ ጋር ማንኛውንም ጥርጣሬ ለማጥፋት በድጋሚ ገለጸው። ምክንያቱም ከተማዋ እጅግ ዝነኛና በየብስም በባሕርም አቻ የማይገኝላት በመሆኗ፣ ለብዙዎች ከተማዋን ማየት ብቻ ለጉዞው ምክንያት ይሆን ነበርና። የሮሜ ሰዎች ስለ ጳውሎስ እንዲህ ያለ (ለታዋቂነት ወይም ከተማዋን ለማየት የመጣ) ጥርጣሬ እንዳያድርባቸው  ጳውሎስ እነርሱን ለራሱ ክብር መጠቀሚያ ሊያደርጋቸው ፈልጎ እንደሆነ እንዳይጠረጥሩት፣ የመምጣቱን ምክንያት ደጋግሞ ያስረዳል። አስቀድሞ "መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ" ብሎ ነበር፤ እዚህ ላይ ደግሞ ይበልጥ ግልጽ በሆነ መንገድ "እንደ ሌሎች አሕዛብ በእናንተ ደግሞ ጥቂት ፍሬ አገኝ ዘንድ" ይላል። ገዥዎቹን ከተገዥዎቹ ጋር፣ የቆንሲላዎቹን (consuls) ድልና ክብር ደግሞ ከአረማውያን (barbarians) ጋር አብሮ ይመድባቸዋል፤ ይህም ያለ ምክንያት አይደለም። የእምነት ክብር ባለበት ዘንድ አረማዊ፣ ግሪካዊ፣ እንግዳ ወይም ባለቤት የለምና፤ ሁሉም ወደ አንዲት የክብር ከፍታ ይወጣሉና።  እዚህ ጋርም አሁንም ትሕትናውን ተመልከት፤ "ላስተምራችሁና ልመክራችሁ" አላለም፤ ነገር ግን ምንድን ነው ያለው? "ፍሬ አገኝ ዘንድ" ነው ያለው። ያውም "ፍሬ" ብቻ ሳይሆን "ጥቂት ፍሬ" በማለት የራሱን ድርሻ ዝቅ ያደርገዋል። ከዚያም ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት እነርሱንም ዝቅ ለማድረግ (ትዕቢታቸው እንዲሰበር) "እንደ ሌሎች አሕዛብ"ይላቸዋል ። "እናንተ ባለጠጎች ስለሆናችሁና ከሌሎች የተሻለ ዕድል ስላላችሁ ብቻ፣ ስለ ሌሎች

ያለኝን ግድሰኝነት[2] አልቀንስም” ማለቱ ነው። እኛ የምንፈልገው ባለጠጎችን ሳይሆን ምዕመናንን ነውና። ያ ረጅም ጺም የሚያሳድጉ፣ የተለየ ልብስ የሚለብሱና ታላላቅ ቃላትን የሚተነፍሱ የግሪክ ጠቢባን አሁን የት አሉ ? መላዋን ግሪክና አረማዊውን ዓለም ያ ይሄ ድንኳን ሰፊ (ጳውሎስ) ወደ ክርስቶስ መለሳቸው። በእነርሱ ዘንድ እጅግ የሚወደሰውና ስሙ የሚነሳው “ፕላቶ” ግን ያንን ሁሉ የታወቀ ዝናውንና ግርማ ሞገስ ያለውን ንግግሩን ይዞ ወደ ሲሲሊ ሦስት ጊዜ ቢመላለስም፣ አንዲትን ንጉሥ እንኳን ማሳመን አልቻለም፤ ይልቁንም ነጻነቱን እስከማጣት ድረስ በውርደት ተመለሰ[3] ።

ይህ ድንኳን ሰፊ ግን ሲሲሊን ወይም ጣሊያንን ብቻ ሳይሆን መላውን ዓለም ዞረ፤ እየሰበከም ቢሆን ከሥራው አላረፈም ነበር፤ ቁርበት ይሰፋል፣ መሥሪያ ቤቱን ያስተዳድር ነበር። ይህም

---

[2] ግድ መሰኘት ለማለት ነው

[3] ታላቁ የግሪክ ፈላስፋ ፕላቶ፣ በሕሊናው የሳላትን «በፈላስፋ የሚመራ ፍጹም መንግሥት» (Ideal State) እውን ለማድረግ ይፈልግ ነበር። ለዚህ ደግሞ ምቹ አጋጣሚ ያገኘ መስሎት ነበር። በሲሲሊ ደሴት (በወቅቱ ሲራኩስ ትባል ነበር) ዲዮናስዮስ (Dionysius) የተባሉ ጨካኝ ነገሥታት (አባትና ልጅ) ያስተዳድሩ ነበር። ፕላቶ እነዚህን ነገሥታት በምክርና በጥበብ ለውጦ፣ ፍጹም እና ፍትሐዊ መሪዎች ለማድረግ ወደ ሲሲሊ ተጓዘ።
ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «ሦስት ቀን» ወይም «ሦስት ጊዜ» ማለቱ ፕላቶ ወደዚያ ያደረጋቸውን ሦስት ዋና ዋና ጉዞዎች ለማመልከት ነው።
ውድቀቱና መከራው
ፕላቶ ንጉሡን ለማሳመንና ጥበብን ለማስተማር የፈለገ ቢሆንም፣ ውጤቱ ግን ፍጹም ውድቀት ነበር፦

- የመጀመሪያው ጉዞ፦ ንጉሡ (ሽማግሌው ዲዮናስዮስ) በፕላቶ ትምህርት ተቆጥቶ፣ ፈላስፋውን በባርነት እንዲሸጥ አደረገው። (በኋላ ጓደኞቹ በገንዘብ ዋጅተው አዳኑት)።
- ሁለተኛውና ሦስተኛው ጉዞ፦ የንጉሡ ልጅ (ወጣቱ ዲዮናስዮስ) ሥልጣን ሲይዝ፣ ፕላቶ እንደገና ሊያስተምረው ተመለሰ። ነገር ግን ንጉሡ ምክሩን አልሰማም፤ ይባስ ብሎም ፕላቶን በቁም እስረኝነት አገተው። ፕላቶ በብዙ መከራና በጓደኞቹ እርዳታ ነው ለጥቂት አምልጦ ወደ አቴንስ የተመለሰው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መልዕክት
ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህንን ታሪክ ያነሳው የሚከተለውን ጥልቅ ነጥብ ለማስረዳት ነው፦
ፕላቶ በዓለም ላይ ካሉ ታላላቅ ፈላስፎች አንዱ ሆኖ፣ የራሱን ጥበብ ተጠቅሞ አንድ ንጉሥ እንኳን ማሳመንና ወደ መልካም መስመር ማምጣት አልቻለም። እንዲያውም ሊገደልና ሊሸጥ ደረሰ።
በአንጻሩ ግን፣ ዓሣ አጥማጆች የነበሩትና የዓለም ፍልስፍና ያልተማሩት ሐዋርያት፣ በክርስቶስ ወንጌል ኃይል ሮማውያንን፣ ነገሥታትንና መላውን ዓለም ማሳመንና መለወጥ ችለዋል።
ይህ የሚያሳየው የሰማያዊው ቃል (የወንጌል) ኃይል ከምድራዊው ፍልስፍና እጅግ የላቀ መሆኑን ነው።

[ **Plato, *Seventh Letter* (*Epistulae VII*)**
- **Plutarch, *Parallel Lives: Life of Dion***
- **Diogenes Laërtius, *Lives and Opinions of Eminent Philosophers* (Book III: Life of Plato)** ]

በቆንሲላዎች ለተወለዱ (ለከበሩ) ሰዎች እንቅፋት አልሆነባቸውም፤ ምክንያቱም መምህራን ለንቀት የሚዳረጉት በሥራቸው ወይም በሙያቸው ሳይሆን፣ በሐሰተኛ ትምህርታቸውና በፈጠራ ወሬያቸው ነውና። በዚህ ምክንያት አቴናውያን (ፈላስፎቹን) እስካሁን ይሳለቁባቸዋል። ይህን ሰው (ጳውሎስን) ግን አረማውያን፣ ሞኞችና ያልተማሩትም ሳይቀሩ ይሰሙታል። ስብከቱ ለሁሉም እኩል የቀረበ ነውና፤ የሥልጣን ልዩነትን፣ የዘር ብልጫን ወይም መሰል ነገሮችን አያውቅም። እምነትን ብቻ ይፈልጋል እንጂ ምርምርን አይሻም። ስለዚህ ወንጌል ጠቃሚና አዳኝ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በቀላሉ የሚቀበሉት፣ የሚወደድ እና ለሁሉም ግልጽ በመሆኑ ሊደነቅ ይገባዋል። ይህም ለሁሉም በረከቱን በጋራ በሚሰጠው በእግዚአብሔር ጥበብ የሆነ ዋና ዓላማ ነው።

እግዚአብሔር ለፀሐይ፣ ለጨረቃ፣ ለምድርና ለባሕር እንዲሁም ለሌሎች ፍጥረታት እንዳደረገው ሁሉ፤ ለባለጸጋውና ለጠቢቡ ትልቅ ድርሻ፣ ለድሃው ደግሞ ትንሽ ድርሻ ሳይሰጥ ለሁሉም እኩል እንዲጠቀሙባቸው እንዳደረገ፤ በወንጌል ስብከትም ረገድ ያደረገው ይህንኑ ነው። እንዲያውም ወንጌል ከእነዚህ (ከፀሐይና ከጨረቃ) ይልቅ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ ለወንጌል ያደረገው እኩልነት ይበልጣል የላቀ ነው።

ለዚህ ነው ጳውሎስ "በአሕዛብ ሁሉ መካከል" የሚለውን ቃል ደጋግሞ የሚጠቀመው። ይህም ለእነርሱ (ለሮሜ ሰዎች) ልዩ አድልዎ እያደረገ ሳይሆን የጌታውን ትእዛዝ እየፈጸመ መሆኑን ለማሳየት ነው። ሁሉንም ወደ እግዚአብሔር ምስጋና እየመራ እንዲህ ይላል፦

ቁጥር ፲፬፦ "ለግሪክ ሰዎችና ለአረማውያንም፥ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም ዕዳ ያለብኝ ነኝ።"

ይህንን ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱም ላይ ተናግሮታል። ይህን ማለቱም ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር ለመስጠት ነው (፩ ቆሮ. ፱፥፲፯)።

ቁጥር ፲፭፦ "ስለዚህም በበኩሌ በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ደግሞ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቻለሁ።"

ኦ! ይህቺ ነፍስ እንዴት ክቡር ናት! እንዲህ ያለ ታላቅ አደጋ ያለበትን ሥራ ተቀብሎ—የባሕር ጉዞውን፣ ፈተናውን፣ ሴራውንና ሁከቱን ሁሉ እያወቀ። ምክንያቱም በክህደት አገዛዝ ሥር ባለች ታላቅ ከተማ ወንጌልን ለመስበክ የሚሄድ ሰው፣ እንደ በረዶ የሚረግፉ ፈተናዎች እንደሚጠብቁት ግልጽ ነበርና። እንዲያውም በዚህች ከተማ በነበረው ጨካኝ ገዥ (በኔሮን) አማካኝነት ነው ሕይወቱን ያጣው። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ታላላቅ መከራዎች እንደሚጠብቁት እያወቀ፣ ጥረቱን ቅንጣት ታህል አልቀነሰም፤ ይልቁንም ይቸኩል፣ ይጨነቅ እና (በመንፈስ) ዝግጁ ነበር። ለዚህም ነው፦ "በበኩሌ... ተዘጋጅቻለሁ" የሚለው።

ቁጥር ፲፮፦ "በወንጌል አላፍርምና።"

ጳውሎስ ሆይ! ምን እያልክ ነው? "በወንጌል እመካለሁ፣ እኮራለሁ፣ እደሰታለሁ" ማለት ሲገባህ፤ አንተ ግን ከዚህ ያነሰውን "አላፍርም"የሚለውን ቃል ትጠቀማለህ? አብዛኛውን ጊዜ እጅግ የከበሩ ነገሮችን ስንገልጽ "አላፍርም" አንልም። ታዲያ ለምን እንዲህ አለ? እርሱ እኮ ከሰማያት በላይ በወንጌል የሚመካ ሰው ነበር። እንዲያውም ለገላትያ ሰዎች ሲጽፍ፦ "ከጌታችን ከኢየሱስ

ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ" (ገላ. ፮፥፲፬)
ብሎ ነበር። ታዲያ እዚህ ጋር ለምን “አላፍርም” አለ?
ምክንያቱም የሮሜ ሰዎች በሀብታቸው፣ በግዛታቸውና በድላቸው ምክንያት በምድራዊ ነገር እጅግ የሚመኩ ነበሩ፤ ነገሥታቶቻቸውንም እንደ አማልክት ይቆጥሩአቸው ነበር፣ እንዲያውም “አማልክት” ብለው ይጠሯቸው ነበር። በዚህም ምክንያት እነርሱን (ነገሥታቱን) በምስሎች፣ በቤተ መቅደሶች፣ በመሠዊያዎችና በመሥዋዕቶች ያመልኩአቸው ነበር። እነርሱ በእንዲህ ያለ ትዕቢት ተወጥረው ሳለ፣ ጳውሎስ ግን ሊሰብክላቸው የሄደው፦ የጸራቢ ልጅ ነው ተብሎ የሚታሰበውን፣ በይሁዳ ተራ በሆነች ሴት ቤት ያደገውን፣ የጦር አጃቢ የሌለውን፣ በሀብት ያልተከበበውን፣ ይልቁንም እንደ ወንጀለኛ ከሌቦች ጋር የሞተውንና ሌሎች ብዙ ውርደቶችን የተቀበለውን ኢየሱስን ነበረ።

ምናልባትም (የሮሜ ሰዎች) ስለ እርሱ ገና የማይነገሩትንና ታላላቅ የሆኑትን ነገሮች ስላላወቁ፣ በልባቸው (ስለ ክርስቶስ) ማፈር ሊመጣባቸው እንደሚችል ስለገመተ፣ ጳውሎስ አስቀድሞ “አላፍርም” አለ፤ እነርሱም እንዳያፍሩ ሊያስተምራቸው ፈለገ። ምክንያቱም በዚህ ባለማፈር ከጸኑ፣ በፍጥነት ወደ መመካትና መኩራት እንደሚሸጋገሩ ያውቅ ነበርና።

አንተም ብትሆን አንድ ሰው፦ “የተሰቀለውን ታመልካለህን?” ቢልህ አትፈር፤ ፊትህንም አትመልስ፤ ይልቁንም በእርሱ ተደሰት፣ ፊትህ ይብራ፣ እንደ ነጻ ሰው ሆነህ ቀና ብለህ እምነትህን መስክር። ደግሞም “የተሰቀለውን ታመልካለህን?” ቢልህ፦ “አዎን! እኔ የማመልከው እንደ እናንተ አማልክት አመንዝራውን፣ አባቱን ተሳዳቢውን ወይም ልጆቹን ገዳዩን አይደለም፤ ነገር ግን በመስቀሉ

የሰይጣናትን አፍ የዘጋውንና ስፍር ቁጥር የሌለውን ቅጥፈታቸውን ያጠፋውን ነው" በለው። መስቀሉ ለእኛ የተደረገው ከማይነገር ሰው ወዳድነት የተነሳ ነውና፤ ለእኛ ያለውን ታላቅ አሳቢነት የሚያሳይ ምልክት ነውና።

በተጨማሪም፣ እነርሱ በታላቅ ንግግርና በውጫዊ ጥበባቸው ተወጥረው ስለነበር፣ ጳውሎስ፦ " እኔ እነዚህን (ፍልስፍናዊ) ምርምሮች ሁሉ ትቼ መስቀሉን ልሰብክ መጣሁ፣ በዚህም አላፍርም፤ ለሚያምኑ ሁሉ ለማዳን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና" ማለቱ ነው። እግዚአብሔር ለመቅጣትም ኃይል አለውና (ግብፃውያንን በቀጣ ጊዜ "ይህች ታላቅ ኃይሌ ናት" ብሏልና (ኢዩ. ፪፥፳፭)፤ ደግሞም "ሥጋንም ነፍስንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩት" ተብሏልና (ማቴ. ፲፥፳፰)። ጳውሎስ ግን "እኔ የመጣሁት የመቅጫና የቅጣት ኃይልን ይዤ ሳይሆን፣ የማዳን ኃይልን ይዤ ነው"ይላል። ታዲያ ወንጌል ስለ ገሃነም፣ ስለ ጨለማና ስለማይሞተው ትል አይናገርምንም? በእርግጥ እነዚህን የምናውቃቸው ከወንጌል ውጭ ከሌላ ከየት ነው? ታዲያ "የማዳን የእግዚአብሔር ኃይል" እንዴት ይባላል? ቀጥሎ ያለውን ሐሳብ አስተውል፦ "ለሚያምኑ ሁሉ፥አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው።"

ምክንያቱም ይህ ለማዳን የሚሆነው ለሁሉም ሳይሆን ለሚቀበሉት (ለሚያምኑት) ብቻ ነው። አንተ ግሪካዊ (አረማዊ) ብትሆንና በሁሉም ዓይነት ክፋት ውስጥ ብትዘፈቅ፣ ስኩቴሳዊ ወይም አረማዊ ብትሆን፣ እንዲያውም እንደ አውሬ ብትሆንና አእምሮ በሌለው ድርጊት ብትሞላ፣ በብዙ ኃጢአት ብትከብድም እንኳ፤ ስለ መስቀሉ ያለውን ቃል ሰምተህ በተጠመቅህ ጊዜ፣ እነዚህን ኃጢአቶች ሁሉ በአንዴ ትደመስሳለህ። ለመሆኑ ለምን

እዚህ ላይ “ “ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው” አለ? ይህ ልዩነት ምን ማለት ነው? እርሱ (ጳውሎስ) ደጋግሞ “መገዘር ቢሆን ወይም አለመገዘር ከንቱ ነው” ሲል አልነበረም? (፩ ቆሮ. ፯፥፲፱) ታዲያ ለምን እዚህ ጋር አይሁዳዊውን ከግሪካዊው አስቀድሞ በመመደብ ልዩነት አደረገ? ይህ የሆነው ለምንድን ነው? “አስቀድሞ” በመባሉ ከአሕዛብ የተሻለ ጸጋ ያገኛል ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም ለዚህም ለዚያም የሚሰጠው ስጦታ ያው አንድ ዓይነት ነውና።

“አስቀድሞ” መባሉ በጊዜ ቅደም ተከተል የተሰጠ ክብር ብቻ ነው። ታላቅ ጽድቅን የመቀበል ብልጫ ኖሮት ሳይሆን፣ ቀድሞ የመቀበል ክብር ብቻ ነው የተሰጠው። ለምሳሌ ለጥምቀት የሚሮጡትን ተመልከት (የተጠመቃችሁ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ)፤ ሁሉም ወደ ጥምቀት ይሮጣሉ፣ ነገር ግን ሁሉም በአንድ ሰዓት አይጠመቁም፤ አንዱ አንደኛ፣ ሌላው ሁለተኛ ይሆናል። ሆኖም አንደኛው ከሁለተኛው የበለጠ ጸጋ አይቀበልም፤ ሁሉም እኩል ስጦታን ያገኛሉ እንጂ። ስለዚህ እዚህ ላይ “አስቀድሞ” መባሉ የቃል ክብር እንጂ የጸጋ ብልጫ አይደለም።

ከዚያም “ለማዳን” ካለ በኋላ፣ ስጦታው በዚህ ብቻ እንደማይቆም በማሳየት ክብሩን ከፍ ያደርገዋል። እንዲህ ይላል፦

ቁጥር ፲፯፦ “ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና።”

ጻድቅ የሆነ ሰው ግን ለዚህ ሕይወት ብቻ ሳይሆን ለሚመጣውም ሕይወት ጭምር ይኖራል። በዚህም የዚህን ሕይወት ብሩህነትና ክብር ይጠቁማል። ምክንያቱም አንድ ሰው ሊድን ቢችልም፣ ያ

ድኅነቱ ግን ያለ እፍረት (በክብር) ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ በንጉሥ ምሕረት ከቅጣት የሚለቀቁ ሰዎች እንደሚድኑት ማለት ነው)። ማንም ሰው ስለ "ድኅነት" በሰማ ጊዜ እንደዚህ ያለ ድኅነት እንዳይመስለው፣ ጳውሎስ "ጽድቅን" ጨመረበት። ያውም ያንተ ጽድቅ ሳይሆን "የእግዚአብሔር ጽድቅ" ነው፤ ይህም የጽድቁን ብዛትና በቀላሉ መገኘቱን ያሳያል።

ምክንያቱም ይህንን ጽድቅ የምታገኘው በድካምና በሥራ ሳይሆን፣ ከላይ በሚሰጥ ስጦታ ነው፤ አንተ ከራስህ የምታበረክተው አንድ ነገር ብቻ ነው፣ እርሱም፦ "ማመን" ነው። ታዲያ አመንዝራው፣ ርኩሱ፣ መቃብር ቆፋሪውና መተተኛው በአንዴ ከቅጣት ነጻ መውጣት ብቻ ሳይሆን "ጻድቅ"፣ ያውም እጅግ የላቀ "የእግዚአብሔር ጽድቅ" ባለቤት ይሆናል የሚለው ንግግር ለሰዎች የማይታመን ሊመስል ስለሚችል፣ ሐሳቡን ከብሉይ ኪዳን ጥቅስ ጋር ያጸናዋል።

በመጀመሪያ በአንዲት አጭር ዐረፍተ ነገር፣ ማስተዋል ለሚችል ሰው ሰፊ የታሪክ ባሕርን ይከፍታል። "ከእምነት ወደ እምነት" ካለ

በኋላ፣ ሰሚውን በብሉይ ኪዳን ወደነበረው የእግዚአብሔር አሠራር ይመራዋል። ይህንንም ወደ ዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ በጥልቅ ጥበብ እንደገለጸው፣ በዚያን ጊዜም ቢሆን ጻድቃኑም ሆኑ ኃጢአተኞቹ የጸደቁት በዚህ መንገድ (በእምነት) እንደነበረ ያሳያል። ለዚህም ነው ስለ ጋለሞታይቱ እና ስለ አብርሃም የጠቀሰው ። እዚህ ጋርም (ጳውሎስ) ወደ ሌላ አስቸኳይ ጉዳይ እየተጣደፈ ስለነበር በጥቆማ ብቻ ካለፈ በኋላ፣ የነቢዩ ዕንባቆምን ቃል በማምጣት የተናገረውን ያጸናል። ነቢዩ፦ "ጻድቅ በእምነት ይኖራል" (ዕን. ፪፥፬) በማለት የሚመጣውን

ሕይወት አስመልክቶ ይጮኻል። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚሰጠን ስጦታ ከሰው ልጅ የምርምር አቅም በላይ ስለሆነ፣ እምነት የግድ ያስፈልገናል።

እምነትን ዝቅ አድርጎ የሚመለከት፣ ትዕቢተኛና ለከንቱ ውዳሴ የሚገዛ ሰው ግን ምንም ዓይነት ፍሬ አያፈራም። መናፍቃን የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ይስሙ፤ የምርምር (የፍልስፍና) ባሕርይ እንዲህ ነውና። መጨረሻ እንደሌለው ቤተ-መንግሥት ወይም እንቆቅልሽ ናቸው፤ አእምሮ በዐለት ላይ እንዳይቆም ያደርጋሉ፤ መነሻቸውም ትዕቢት ነው። በእምነት ለመመራት ስለሚያፍሩና ሰማያዊውን ነገር እንደማያውቁ መታየት ስለሚከብዳቸው፣ በብዙ ምርምሮች ትብያ ውስጥ ራሳቸውን ይዘፍቃሉ።

አንተ ምስኪን እና ተላላ ሰው ሆይ! “ሰማይ እና ምድር እንዴት ተፈጠሩ?” ብሎ አንድ ሰው ቢጠይቅህ—ለምንስ ሰማይና ምድር እላለሁ?— አንተ ራስህ እንዴት እንደተወለድክ፣ እንዴት እንደተመገብክና እንዳደግክ ብትጠየቅና መልሱን ባታውቅ አታፍርም ? ታዲያ ስለ አንድያ

ልጁ (ስለ ወልድ) አንድ ነገር ሲነገር፣ ሁሉንም ነገር አለማወቅ ላንተ የማይገባ መስሎ ስለሚታይህ በማፈር ራስህን ወደ ጥፋት ጉድጓድ ውስጥ ትከታለህን? እንዲያውም ክርክር እና ያለ ቦታው የሚደረግ ምርምር የማይገቡ ነገሮች ናቸው። ስለ ትምህርተ መለኮት ብቻ ለምን እናገራለሁ? አሁን ካለብን የሕይወት ብክነት እንኳን በእምነት ካልሆነ በቀር በሌላ መንገድ አላመለጠንም።

የቀደሙት ሁሉ የከበሩት በዚህ ነው፤ አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ የከበሩት በዚህ ነው። በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የነበሩ ጋለሞቶች የዳኑት በዚህ ነው። “ጋለሞታይቱ ረዓብ ሰላዮችን

በሰላም ስለ ተቀበለቻቸው ከማይታዘዙ ጋር በእምነት አልጠፋችም” (ዕብ. ፲፩፥፴፩) ተብሏልና። እርሷ በልቧ፦ “እነዚህ ተማርከው የመጡ፣ የተሰደዱና እንደ ዘላን የሚኖሩ ሰዎች እኛን ቅጥርና ግንብ ያለን ሰዎችን እንዴት ሊያሸንፉን ይችላሉ?” ብላ ብታስብ ኖሮ፣ ራሷንም እነርሱንም ባጠፋች ነበር። ያመለጡት ሰዎች አባቶች (የእስራኤል ሰዎች) የደረሰባቸው ግን ይኸው ነበር። ግዙፎቹንና ረጅም ሰዎቹን ባዩ ጊዜ “እንዴት ድል እናደርጋለን?” ብለው ሲመራመሩ፣ ያለ ጦርነትና ያለ ሰልፍ ሁሉም በምድረ በዳ ጠፉ። የክህደት (ያለማመን) ጉድጓድ ምን ያህል ጥልቅ እንደሆነ፣ የእምነት ግንብስ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ አየህ? አንዱ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ ጥፋት ሲያወርድ፣ ሌላኛው ግን ጋለሞታይቱን ማዳን ብቻ ሳይሆን የእንዲህ ያለ ታላቅ ሕዝብ ጠባቂ (አማላጅ) አደረጋት! እንግዲህ ይህንንና ከዚህ በላይ ያለውን ካወቅን በኋላ፣ እግዚአብሔርን ፈጽሞ  አንጠይቀው፤ ነገር ግን የሚሰጠንን ማንኛውንም ነገር በትሕትና እንቀበል። የታዘዝነው ነገር ለሰው ልጅ አእምሮ ስህተት መስሎ ቢታይም እንኳ፣ በጥቃቅን ነገሮችና በምርምር ጥያቄዎች

ውስጥ አንግባ። እስኪ ልጠይቃችሁ፦ አንድ አባት የገዛ አንድያና የቃል ኪዳን ልጁን በገዛ እጁ እንዲሰዋ ከመታዘዝ በላይ ምን የሚከብድ ነገር አለ? (ዘፍ. ፳፪፥፫)። ሆኖም ግን ያ ጻድቅ ሰው (አብርሃም) ይህን እንዲያደርግ በተታዘዘ ጊዜ፣ ምንም ዓይነት ጥርጣሬና ጭንቀት ውስጥ አልገባም፤ ይልቁንም ያዘዘውን አምላክ ክብር በመመልከት ብቻ ትእዛዙን ተቀበለ።

ደግሞም ሌላውን ሰው ተመልከቱ፤ አንድ ነቢይን እንዲመታ በእግዚአብሔር ታዝዞ ነበር። ነገር ግን ትእዛዙ ምክንያታዊ መስሎ

ስላልታየው ጥርጣሬ ውስጥ በገባና በቀላሉ ባለመታዘዙ ምክንያት፣ እጅግ በጸና ሁኔታ ተቀጣ (፩ ነገ. ፳፥፴፭-፴፮)። ያ የመታው ሰው ግን መልካም ምስክርነትን አገኘ። ሳኦልም ቢሆን ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጭ ሰዎችን በማዳኑ (በማትረፉ) ከመንግሥቱ ወደቀ፤ ዳግም ሊመለስ በማይችል ሁኔታም ተቀጣ። ከእነዚህም ውጭ ሌሎች ብዙ ምሳሌዎችን ማግኘት ይቻላል።

ከእነዚህ ሁሉ የምንማረው፣ ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ፈጽሞ ምክንያት እንዳንፈልግ ነው፤ ነገር ግን መገዛትና መታዘዝ ብቻ ይገባናል። እግዚአብሔር በሚያዘው ነገር ላይ ጥርጣሬ ማሳደር እንዲህ አደገኛ ከሆነና በምርምር ለሚጠይቁትም እንዲህ ያለ ጽኑ ቅጣት የሚጠብቃቸው ከሆነ፤ ከእነዚህ ይልቅ እጅግ ምስጢራዊና አስፈሪ በሆኑት ነገሮች ላይ ለሚመራመሩት ምን ዓይነት ምክንያት ይኖራቸዋል? ለምሳሌ፦ “ ወልድን እንዴት ወለደው? በምን ዓይነት መንገድ? ባሕርይውስ ምንድን ነው?” እያሉ ለሚመራመሩት።

እንግዲህ ይህንን ካወቅን በኋላ፣ የበረከቶች ሁሉ እናት የሆነችውን እምነትን በታላቅ በጎነት እንቀበል። ይኸውም ጸጥ ባለ ወደብ ውስጥ እንደምትጓዝ መርከብ ሆነን፣ ትምህርታችንን የቀና አድርገን እንድንጠብቅ፣ ሕይወታችንንም በቀጥተኛ መንገድ እየመራን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰው ወዳድነት ያንን

የዘላለም በረከት እንድንወርስ ነው። ክብር ለእርሱ ይሁን፤ ከእርሱ ጋር ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ዛሬም ዘወትርም እስከ ዘላለም ድረስ  አሜን።

# ድርሳን ሦስት ( Homily III )

ሮሜ ፩፥፲፰፦ "እውነትን በዓመፅ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቊጣ ከሰማይ ይገለጣልና።"

የጳውሎስን ጥበብ ተመልከት፤ በመጀመሪያ በለዘቡና ደስ በሚሉ ነገሮች ካበረታታቸው በኋላ፣ አሁን ደግሞ ንግግሩን ወደሚያስፈሩ ነገሮች ይመልሳል። ወንጌል የድኅነትና የሕይወት ምክንያት እንደሆነ፣ የእግዚአብሔር ኃይል እንደሆነ፣ ጽድቅንና መዳንን እንደሚሰጥ ከተናገረ በኋላ፤ አሁን ደግሞ ወንጌልን ቸላ የሚሉትን ሊያስፈራቸው የሚገባውን ነገር ይጠቅሳል።

ምክንያቱም አብዛኛው ሰው በሚሰጠው በጎ ተስፋ ከመሳብ ይልቅ፣ በሚመጣው ሕመም (ቅጣት) ፍርሃት መመለስ ይቀለዋልና፤ ጳውሎስ በሁለቱም በኩል ይስባቸዋል። እግዚአብሔርም ቢሆን መንግሥተ ሰማያትን ቃል ከመግባት ጋር ገሃነምን ያስፈራራው ለዚህ ነው። ነቢያትም ከአይሁድ ጋር ሲነጋገሩ መልካሙንና ክፉውን እያቀላቀሉ ይናገሩ ነበር።

ጳውሎስም ንግግሩን የሚለዋውጠው ያለ ምክንያት አይደለም፤ መጀመሪያ መልካሙን፣ ቀጥሎ ደግሞ ክፉውን ያስቀምጣል። ይህም መልካሙ ነገር ከእግዚአብሔር ቀዳሚ ፈቃድ የመጣ መሆኑን፣ ክፉው (ቅጣቱ) ግን ከሰዎች ወደ ኋላ ማፈግፈግና ክፋት የመጣ መሆኑን ለማሳየት ነው። ነቢዩም፦ "እሺ ብትሉና

ብትሰሙኝ÷ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እምቢ ብትሉና ባትሰሙኝ ግን÷ ሰይፍ ይበላችኋል" (ኢሳ. ፩÷፲፱-፳) በማለት መልካሙን አስቀድሟል። ጳውሎስም ንግግሩን እንዲህ ይመራዋል። “ክርስቶስ የመጣው ይቅርታን፣ ጽድቅንና ሕይወትን ይዞ ነው፤ ይህም የሆነው ዝም ብሎ ሳይሆን በመስቀል ነው” ማለቱ ነው። ይህ ደግሞ ታላቅና ድንቅ ነገር ነው፤ ምክንያቱም እነዚህን ስጦታዎች መስጠት ብቻ ሳይሆን፣ ስለ እነርሱም መከራን ተቀብሏልና። እንግዲህ እነዚህን ስጦታዎች በትዕቢት ብትንቁ፣ ቅጣት ይጠብቃችኋል” ይላል።

አነጋገሩን እንዴት ከፍ እንደሚያደርግም ተመልከት፦ "የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣል" ይላል። ታዲያ ይህ እንዴት ይታወቃል? ይህን የሚጠይቀው አማኝ ከሆነ፣ የክርስቶስን ምስክርነት (ቃላት) እንነግረዋለን፤ ነገር ግን አረማዊ (ግሪካዊ) ከሆነ፣ ጳውሎስ ቀጥሎ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ በሚናገረው ቃል ዝም ያሰኘዋል። ይህም እነርሱ ራሳቸው በሚያደርጉት ድርጊት የማይካድ ማስረጃ በማምጣት ነው።

በጳውሎስ ዘንድ እጅግ አስደናቂው ነጥብ ይህ ነው፦ እውነትን የሚቃወሙ ሰዎች ራሳቸው በየዕለቱ በሚያደርጉትና በሚናገሩት ነገር፣ ለእውነት ትምህርት ምስክሮች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይህንን ወደፊት በዝርዝር እናየዋለን፤ ለአሁኑ ግን የቀረበልንን እንመልከት፦

"የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣል"። እንዲያውም እዚህ ምድር ላይ እንኳ ብዙውን ጊዜ (የእግዚአብሔር ቁጣ) በራብ፣ በቸነፈርና በጦርነት ይገለጣል፤ እያንዳንዱ ሰው ለየብቻው ወይም ሁሉም በአንድነት ይቀጣሉና። ታዲያ በዚያን ጊዜ (በመጨረሻው

ፍርድ) የሚመጣው አዲስ ነገር ምንድን ነው? ቅጣቱ እጅግ የላቀ፣ ለሁሉም የሚሆንና አሁን ባለው ሕግ የማይመራ መሆኑ ነው።

አሁን የሚሆነው ነገር ሁሉ ለተግሣጽና ለለውጥ ነው፤ ያን ጊዜ የሚሆነው ግን ለበቀል ነው። ቅዱስ ጳውሎስም፦ "ከዓለም ጋር እንዳንኮነን አሁን እንገሠጻለን" (፩ ቆሮ. ፲፩÷፴፪) በማለት ይህንን አሳይቷል። አሁን ግን ለብዙዎች እንዲህ ያሉት መከራዎች ከላይ ከሚመጣ ቁጣ ሳይሆን፣ ከሰዎች ክፋት የሚመጡ ይመስላቸዋል። ነገር ግን ፈራጁ በዚያ በሚያስፈራው ወንበር ላይ ተቀምጦ፣ አንዳንዶቹን ወደ እሳት እቶን፣ ሌሎቹን ወደ ውጭው ጨለማ፣ ሌሎቹን ደግሞ ወደማይታገሡና ወደማያልቁ ቅጣቶች እንዲወሰዱ በሚያዝበት ጊዜ የእግዚአብሔር ቅጣት ግልጽ ይሆናል።

ታዲያ ለምን ጳውሎስ "የእግዚአብሔር ልጅ ከአእላፋት መላእክት ጋር ይመጣል፣ እያንዳንዱንም ይጠይቃል" ብሎ በግልጽ ከመናገር ይልቅ፦ "የእግዚአብሔር ቁጣ ይገለጣል" በማለት ብቻ ተናገረ? ሰሚዎቹ ገና አዲስ ስለነበሩ፣ መጀመሪያ እነርሱ ዘንድ ተቀባይነት ባላቸውና በሚያውቋቸው ነገሮች ይስባቸዋል። በተጨማሪም፣ እዚህ ጋር የግሪክ ሰዎችን (አረማውያንን) ለመቃወም የፈለገ ይመስለኛል። ለዚህ ነው ንግግሩን ከዚህ የጀመረው፤ በኋላ ግን ስለ ክርስቶስ ፍርድ ሐሳቡን ያስተዋውቃል።

"እውነትን በዓመፅ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ..." እዚህ ጋር የኃጢአተኝነት መንገዶች ብዙ እንደሆኑ፣ የእውነት መንገድ ግን አንድ መሆኑን ያሳያል። ስህተት የተለያየ፣ ብዙ መልክ ያለውና የተወሳሰበ ነው፤ እውነት ግን

አንዲት ናት። ስለ ትምህርተ መለኮት (doctrines) ከተናገረ በኋላ፣ ስለ ሰዎች ዓመፅ በመጥቀስ ስለ ሕይወት ይናገራል።

ዓመፅም ብዙ ዓይነት ነውና። አንዱ በገንዘብ ረገድ ጎረቤቱን የሚበድልበት ነው፤ ሌላው ደግሞ በሴቶች ረገድ፣ የገዛ ሚስቱን ትቶ የሌላውን ትዳር የሚደፍርበት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ይህንንም “መበደል/ማታለል” ብሎ ይጠራዋል፦ "ማንም በዚህ ነገር አይተላለፍ ወንድሙንም አያታልል" (፩ ተሰ. ፬፥፮) እንዳለ። ሌሎች ደግሞ በሚስት ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ባያደርሱም፣ በባልንጀራቸው ስም (ዝና) ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፤ ይህም ዓመፅ ነው። "መልካም ስም ከብዙ ባለጠግነት ይሻላል" (ምሳሌ ፳፪፥፩) ተብሏልና።አንዳንዶች ግን ጳውሎስ ይህንን የተናገረው ስለ ስለ ሐሰት ትምህርት ነው ይላሉ። ሆኖም ግን ለሁለቱምተነግሯል ቢባል የሚከለክል ነገር የለም። “እውነትን በዓመፅ መያዝ” ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግን ከሚቀጥለው ሐሳብ ተረዳ።

ቁጥር ፲፱፦ "እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና።"

ነገር ግን ይህንን (ለእግዚአብሔር የሚገባውን) ክብር ለእንጨትና ለድንጋይ ሰጡ። ለምሳሌ፦ የአንድ ንጉሥ ንብረት አደራ የተሰጠውና ያንንም ንብረት ለንጉሡ ክብር እንዲያውለው የታዘዘ ሰው፣ ያን ንብረት ለሌቦች፣ ለጋለሞቶችና ለጠንቋዮች ቢበትነው፣ በእነርሱም ላይ የንጉሡን ግምጃ ቤት ቢያባክን፤ በንጉሡ ላይ ታላቅ በደል እንደፈጸመ ተቆጥሮ ይቀጣል።

ልክ እንደዚሁ፣ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ክብሩ ያለውን ዕውቀት ከተቀበሉ በኋላ ያንን ክብር ለጣዖታት የሰጡት ሰዎች “እውነትን በዓመፅ ያዙ” ። በዕውቀቱ ላይ ግፍ ፈጸሙ፤ ዕውቀቱን ለሚገባው

ዓላማ ስላልተጠቀሙበት። አሁን የተናገርኩት ግልጽ ሆነላችሁ ወይስ ይበልጥ ላብራራው? ምናልባት ጥቂት መጨመር የሚያስፈልግ ይመስላል። እዚህ ጋር የተባለው ምንድን ነው? እግዚአብሔር ስለ ራሱ ያለውን ዕውቀት ከመጀመሪያውኑ በሰዎች ውስጥ አኑሮታል። እነርሱ ግን ይህን ዕውቀት ለእንጨትና ለድንጋይ ሰጡት፤ በዚህም በእውነት ላይ እስከሚችሉት ድረስ ግፍ ፈጸሙ። እውነት ግን የራሷ የማይለወጥ ክብር ስላላት እንደጸናች ትኖራለች። ጳውሎስ ሆይ! ይህንን ዕውቀት በእነርሱ ውስጥ እንዳኖረው በምን ይታወቃል?' ቢባል፤ " ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና" ይላል። ይህ ግን አባባል እንጂ ማስረጃ  አይደለም። "እስኪ ማስረጃውን አቅርብ፤ እግዚአብሔርን ማወቅ ለእነርሱ ግልጽ እንደነበረና እነርሱ ግን ሆን ብለው ወደ ጎን እንዳሉ አሳየኝ" ቢባል መልሱ ምንድን ነው? ታዲያ እንዴት ግልጽ ሆነላቸው? ከላይ ድምፅ ላከላቸውን? በፍጹም! ነገር ግን ከድምፅ ይልቅ ይበልጥ ወደ እርሱ ሊስባቸው የሚችለውን ነገር አደረገ፤ ይኸውም ፍጥረትን (Creation) በፊታቸው አስቀመጠ። በዚህም ጠቢቡም፣ ያልተማረውም፣ ኩቴሳዊውም ስኩቴሳዊውም ሆነ አረማዊው በሚታዩት ነገሮች ውበት አማካኝነት ፈጣሪን አይተው ወደ እግዚአብሔር ይወጡ ዘንድ ነው  ለዚህ ነው፦

ቁጥር ፳፦ "የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሰሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና።"

ይህንን ነቢዩም፦ "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ" (መዝ. ፲፱፥፩) በማለት ተናግሮታል። በዚያን ቀን (በፍርድ ቀን)

አረማውያን ምን ይላሉ? " አንተን አናውቅህም ነበር" ይላሉን? ሰማያት በእይታ ድምፃቸውን ሲያሰሙ፣ የሁሉ ነገር በሚገባ የተደራጀ ስምምነት ከመለከት ይልቅ ይበልጥ ግልጽ በሆነ መንገድ ሲናገር አልሰማችሁም ነበርን? የሌሊትና የቀን ሰዓታት ሳይዛነፉ ሲፈራረቁ፣ የክረምት፣ የጸደይና የሌሎች ወቅቶች ሥርዓት ጸንቶ ሲቆይ፣ ባሕር እንኳ በማዕበልና በሞገድ ብትናወጥም ዳርቻዋን ጠብቃ ስትገዛ አላያችሁም ነበርን? ፍጥረት ሁሉ በሥርዓት ጸንቶ በመቆሙ፣ በውበቱና በታላቅነቱ ስለ ፈጣሪው ድምፁን ከፍ አድርጎ አይሰብክም ነበርን? ጳውሎስ እነዚህንና ከእነዚህም በላይ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ጠቅልሎ ሲናገር፦ "የማይታየው ባሕርዩ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያል" ይላል።

የማይታየው ባሕርዩ፣ የዘላለም ኃይሉና አምላክነቱ ከተሠሩት ታውቆ ይታያል፤ "ስለዚህም ምክንያት የላቸውም"። እግዚአብሔር ግን እነዚህን ታላላቅ የትምህርት ሥርዓቶች (ፍጥረታትን) በፊታቸው ያስቀመጠው ያለ ምክንያት እንዲቀሩ ለማድረግ ሳይሆን፣ እርሱን ያውቁ ዘንድ ነው። ነገር ግን እርሱን ባለማወቃቸው ራሳቸውን ምክንያት አሳጡ። ይህንንም መከላከያ ምክንያት ማጣታቸውን ለማሳየት እንዲህ ይላል፦

### ቁጥር ፳፩፦ "እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን አላከበሩትምና።"

ይህ የመጀመሪያውና ትልቁ ክስ ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ጣዖታትን ማምለካቸው ነው። ነቢዩ ኤርምያስም ሲከሳቸው፦ "ሕዝቤ ሁለት ክፉ ነገሮችን አድርገዋልና፤ የሕያው ውኃ ምንጭ የሆንሁትን እኔን ትተውኛል፥ ውኃም የማይይዙትን የተቀደዱ

ጉድጓዶች ለራሳቸው ቆፍረዋል" (ኤር. ፪፥፲፫) ብሏል።
እግዚአብሔርን ያውቁ እንደነበር እና ዕውቀታቸውንም ለሚገባው ነገር እንዳልተጠቀሙበት ለማሳየት፣ "አማልክት" እንዳሉ ማመናቸውን እንደ ማስረጃ ያቀርባል። ለዚህ ነው "እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን አላከበሩትም" ያለው።

ታዲያ ወደዚህ ዓይነት ስንፍና እንዲወድቁ ያደረጋቸው ምክንያት ምንድን ነው? ሁሉንም ነገር በገዛ ምርምራቸውና በሐሳባቸው ላይ መመካታቸው ነው። ጳውሎስ ግን ይህንን "በሐሳባቸው ከንቱ ሆኑ" በሚል እጅግ በሚሰቀጥጥ ቃል ይገልጸዋል።

"በሐሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውልም ልባቸው ጨለመ"።

ጨረቃ በሌለበት ጨለማ ሌሊት፣ አንድ ሰው የማያውቀውን መንገድ ለመሄድ ወይም በማያውቀው ባሕር ላይ ለመጓዝ ቢሞክር፣ ወደፈለገበት መድረስ ቀርቶ በፍጥነት ይጠፋል። ልክ እንደዚሁ፣ እነርሱም ወደ ሰማይ የሚወስደውን መንገድ ለመሄድ ሲሞክሩ፣ ከራሳቸው ሊያበራ የሚገባውን ብርሃን (እምነትን) አጥፍተው፣ በምትኩ በገዛ ሐሳባቸው ጨለማ ላይ ተመኩ። ሥጋ የሌለውን (ረቂቁን አምላክ) በሥጋዊ አካላት ውስጥ፣ መልክ የሌለውን ደግሞ በምስሎች ውስጥ ፍለጋ ሲሄዱ፣ እጅግ አሳዛኝ የሆነ የመርከብ መሰበር ደረሰባቸው። ከዚህም በተጨማሪ ጳውሎስ ለስህተታቸው ሌላ ምክንያት ይጠቅሳል፦

ቁጥር ፳፪፦ "ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ።"

ስለ ራሳቸው ታላቅ ግምት (ትዕቢት) ስለነበራቸውና እግዚአብሔር ያዘዛቸውን መንገድ መከተል ስላልፈለጉ፣

ወደማያስተውል የሐሳብ ማዕበል ውስጥ ሰመጡ። ይህ ማዕበል ምን ያህል አሳዛኝ እንደሆነና መከላከያም እንደሌላቸው ለማሳየት እንዲህ ይላል፦

ቁጥር ፳፫፦ "የማይጠፋውንም የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ።"

እንግዲህ ክሱ አራት ደረጃዎች አሉት፦

1. መጀመሪያ፦ እግዚአብሔርን አላገኙትም (አላወቁትም)።

2. ሁለተኛ፦ እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚያስችሉ ታላላቅና ግልጽ የሆኑ ማስረጃዎች (ፍጥረታት) በፊታቸው እያሉ አላወቁትም።

3. ሦስተኛ፦ ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ ጥበበኞች ነን" ማለታቸው።

4. አራተኛ፦ ያንን የተከበረ አምላክ አለማግኘታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ክብሩን ዝቅ አድርገው በምስሎች መለወጣቸው ነው።"

ያንን የተከበረ አምላክ ወደ አጋንንት፣ ወደ ድንጋይና ወደ እንጨት አወረዱት። ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልዕክቱም ትዕቢታቸውን ሰብሮታል፤ ነገር ግን እዚያ ጋር ያደረገው እዚህ ካለው በተለየ መንገድ ነው። እዚያ ጋር በመስቀሉ ኃይል መታቸው፤ "የእግዚአብሔር ሞኝነት ከሰው ይልቅ ይበልጣል" (፩ ቆሮ. ፩÷፳፭) በማለት። እዚህ ጋር ግን ምንም ዓይነት ንጽጽር ሳይጠቀም፣ የገዛ ጥበባቸውን ለብቻው አውጥቶ ያላግጥበታል (ይተቸዋል)፤ ጥበባቸው ስንፍናና ከንቱ ጉራ መሆኑንም ያሳያል። ከዚያም እግዚአብሔርን የማወቅ ዕድሉ እያላቸው እንዴት በክህደት አሳልፈው እንደሰጡት እንድታውቅ፦ "ለወጡ" ይላል።

አንድ ሰው “ለወጠ” የሚባለው የሚለውጠው ነገር (ቀድሞ የነበረው እውነት) ሲኖረው ነው። እነርሱ ግን ከተሰጣቸው ወሰን በላይ ፈልገው አዳዲስ ነገሮችን ለማግኘት ሞከሩ፤ በዚህም ምክንያት ከነበራቸው እውነት ተባረሩ። የአረማውያን (የግሪኮች) ጠባይ ሁልጊዜ አዳዲስ ፈጠራዎችንና ፍልስፍናዎችን መመኘት ነውና። ለዚህም ነው እርስ በእርሳቸው የተቃረኑት፤ አሪስቶትል በፕላቶ ላይ ተነሣ፣ ስቶይኮችም (Stoics) በእርሱ ላይ ተከራከሩ፣ አንዱ ከሌላው ጋር ጠላት ሆነ።

ስለዚህ አንድ ሰው በጥበባቸው ሊደነቅባቸው አይገባም፤ ይልቁንም በዚህ ባመጡት ጥበብ ደንቆሮዎች ስለሆኑ ሊጸየፋቸውና ሊጠላቸው ይገባል። ምክንያቱም በገዛ አእምሯቸው ምርምር በምክንያታዊነት ድርድር እና በአሳሳች ንግግሮች ባይመኩ ኖሮ፣ አሁን የደረሰባቸው ውድቀት አይደርስባቸውም ነበር። ከዚያም ክሱን ይበልጥ ለማጠንከር፣ የጣዖት አምልኮአቸውን በሙሉ መሳለቂያ ያደርገዋል።

በመጀመሪያ ደረጃ፣ “መለወጥ” (እግዚአብሔርን በሌላ መተካት) በራሱ የሚያስቅና የሚያሳፍር ነው። ነገር ግን ወደ ምን እንደለወጡት ስታይ ደግሞ ምንም ዓይነት መከላከያ ሰበብ የላቸውም። ምን ለማግኘት ነው የለወጡት? ለእግዚአብሔር ክብር የሚገባውንስ ለማን ሰጡት? ስለ እግዚአብሔር ሊኖራቸው የሚገባው እውነት፦ እርሱ አምላክ እንደሆነ፣ የሁሉ ጌታ እንደሆነ፣ ያልነበሩትን እንደፈጠረ፣ በሁሉ ላይ እንደሚገዛ እና ለፍጥረቱ እንደሚራራ ማወቅ ነበር። “የእግዚአብሔር ክብር” የሚባለው ይህ ነውና። ታዲያ ይህን ክብር ለማን ሰጡ? ቢያንስ ለሰው እንኳ አልሰጡትም፤ ይልቁንም “ለሚጠፋ ሰው ምስል” ሰጡት። በዚህም

አልቆሙም፤ ወደ እንስሳት፣ እንዲያውም ወደ እንስሳት ምስሎች ወረዱ።

እንግዲህ የጳውሎስን ጥበብ ተመልከት፤ እንዴት ሁለቱን ጽንፎች እንደወሰደ። እጅግ ከፍተኛ የሆነውን "አምላክን" እና እጅግ ዝቅተኛ የሆኑትን "ተሳቢ እንስሳትን" (ወይም የእነርሱን ምስሎች) ጎን ለጎን አስቀመጣቸው። ይህም ግልጽ የሆነ እብደታቸውን ለማሳየት ነው። ከሁሉ በላይ ለሆነውና ለማይነጻጸረው አምላክ ሊሰጡት የሚገባውን እውቀት፣ ከሁሉ በታች ለሆነውና ለማይረባው ነገር ሰጡት። አንድ ሰው፦ "ይህ ከፈላስፎች ጋር ምን አገናኘው?" ሊል ይችላል። እንዲያውም እኔ የተናገርኩት ከማንም በላይ እነርሱን ይመለከታቸዋል! ምክንያቱም እነዚህን (የጣዖት) ነገሮች የፈጠሩትን ግብፃውያንን እንደ መምህራቸው አድርገው ይዘዋልና።

ከሌሎቹ ይልቅ እጅግ የተከበረ የሚመስለው ፕላቶ እንኳ በእነዚህ መምህራኑ ይመካል። መምህሩ ሶቅራጥስ ደግሞ ለእነዚህ ጣዖታት በድንቁርና ይገዛ ነበር፤ ለምሳሌ ሊሞት ሲል ለአስቀሊባዮስ (Esculapius) "ዶሮ እንዲሠዋለት" ያዘዘው እርሱ ነው[4]። በዚህ

---

[4] ታላቁ የግሪክ ፈላስፋ ሶቅራጥስ በአቴንስ መኳንንትና ዳኞች አማካኝነት አዳዲስ አማልክትን በማስተዋወቅና ወጣቶችን በመበከል ተከሶ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ነበር። ፍርዱንም ለመፈጸም የሄምሎክ የተባለውን መርዝ ጠጥቶ በሞት አፋፍ ላይ በነበረበት ሰዓት፣ ዙሪያውን ከበውት ለነበሩት ደቀ መዛሙርቱና ወዳጆቹ የመጨረሻ የሚባለውን ታዋቂ ቃል ተናገረ። ሶቅራጥስ ወደ ወዳጁ ወደ ክሪቶን ዞር ብሎ «ክሪቶን ሆይ፣ ለአስቅሊፒዮስ አንድ ዶሮ ዕዳ አለበት፤ እባክህ ይህንን መሥዋዕት ሳትረሳ ክፈልልኝ» አለው። አስቅሊፒዮስ የሚባለው አካል በግሪካውያን ዘንድ የሕክምና እና የፈውስ አምላክ ተብሎ የሚታመን ጣዖት ሲሆን፣ በወቅቱ የነበረው ባህል ደግሞ አንድ ሰው ከበሽታና ከስቃይ ሲድን ለዚህ ጣዖት ዶሮ ማረድን ይጠይቅ ነበር። ሶቅራጥስም ሞትን ከዚህ ምድራዊ ሥጋና ከዓለም ስቃይ ተለይቶ ወደ እውነተኛው ነጻነት መሸጋገሪያ ወይም መፈወሻ አድርጎ ስለቆጠረው፣ እንደ ምስጋና ዓይነት መሥዋዕት እንዲቀርብለት መፈለጉ ነበር።
ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህንን ታሪክ በትርጓሜው ላይ ያመጣው የዓለም ጥበብ ያለ ክርስቶስ ወንጌል ምን ያህል ጨለማ ውስጥ እንደነበረች ለአንባቢው ለማሳየት ነው። በዓለም ላይ ካሉ የሰው ልጆች ሁሉ የላቀ አእምሮና ፍልስፍና አለው የሚባለው ሶቅራጥስ እንኳ፣ በሕይወቱ የመጨረሻ ሰዓትና በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ለጣዖት የሚሆን ዶሮ እረዱልኝ ከማለት ያለፈ እውነተኛ የፈጣሪ እውቀት አልነበረውም። ሊቁ ይህንን የታሪክ አውድ በመጥቀስ፣ የዓለም ታላላቅ ፈላስፎች በገዛ ጥበባቸው ራሳቸውን እንኳ ከጣዖት ድንቁርና ማውጣት እንዳልቻሉና በአንጻሩ ግን ያልተማሩት ሐዋርያት በክርስቶስ ወንጌል ኃይል መላውን ዓለም ከዚህ የጣዖት ባርነት ነጻ እንዳወጡት በጥልቀት ያስረዳል።

**[ Plato, *Phaedo* (118a)**
**Diogenes Laërtius, *Lives and Opinions of Eminent Philosophers* (Book II: Life of Socrates) ]**

የአስቀሊባዮስ መቅደስ ውስጥ ደግሞ የእነዚህ አራዊትና ተሳቢዎች ምስሎች ነበሩ። አፖሎና ባኩስ (Apollo and Bacchus) ከእነዚህ ተሳቢዎች ጋር አብረው ሲመለኩ ማየት የተለመደ ነበር። እንዲያውም አንዳንዶቹ ፈላስፎች በሬዎችን፣ ጊንጦችን፣ ዘንዶዎችንና ሌሎችንም ከንቱ ነገሮች እስከ ሰማይ ድረስ ከፍ ከፍ አደረጉ (በከዋክብት ስም ሰየሟቸው)። ሰይጣን በየቦታው ሰውን ከተሳቢ እንስሳት ምስል ፊት ለማንበርከክ እጅግ ይተጋ ነበርና፤ እግዚአብሔር ከሰማያት በላይ ከፍ ሊያደርገው የወደደውን ሰው፣ አእምሮ ከሌላቸው ነገሮች ሁሉ በታች ሊያሰልፈው ይጥራልና።

የእነርሱ ቁንጮ የሆኑት ሰዎች እንኳ በዚህ ወቀሳ ውስጥ እንደሚወድቁ ከሌሎችም ማስረጃዎች ማየት ትችላለህ። ፕላቶ የገጣሚዎችን ሐሳብ ሰብስቦ “ስለ እግዚአብሔር ጉዳይ ትክክለኛ ዕውቀት ስላላቸው ልናምናቸው ይገባል” ካለ በኋላ፣ ከእነዚህ ዘግናኝ ከንቱነቶች በቀር ምንም የሚያቀርበው ነገር የለም፤ ከዚያም ይህንኑ ፍጹም አስቂኝ የሆነ ተላላነት “እውነት ነው” ብለን እንድንይዝ ይነግረናል።

ቁጥር ፳፬፦ “ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩስነት እግዚአብሔር አሳልፎ ሰጣቸው።”

እዚህ ጋር ጳውሎስ የሥነ-ምግባር ሕጎች መዛባት መንስኤው ክህደት መሆኑን ያሳያል።

“አሳልፎ ሰጣቸው” ማለት ደግሞ “ተዋቸው” ማለት ነው። ለምሳሌ በአንድ ጦርነት ላይ ያለ አዛዥ፣ ውጊያው ሲበረታበት ጦሩን ትቶ ቢሄድ፣ ወታደሮቹን ለጠላት አሳልፎ ሰጠ ይባላል፤ ይህ

ግን ወታደሮቹን በግፍ ወደ ጠላት በመግፋት ሳይሆን፣ የእርሱን ድጋፍና እርዳታ በመንፈጉ ብቻ ነው።

እግዚአብሔርም እንዲሁ አደረገ፤ ከእርሱ የሚመጣውን ለመቀበል ያልፈለጉትንና ቀድመው ከእርሱ የራቁትን ሰዎች ተዋቸው። እግዚአብሔር ግን የእርሱን ድርሻ በሙሉ ፈጽሞ ነበር። እስኪ አስቡ፦ እንደ መማሪያ እንዲሆናቸው "ዓለምን" በፊታቸው አስቀመጠ፤ የሚያስፈልገውን ማስተዋል የሚችል አእምሮና "ምክንያት" (reason) ሰጣቸው። የዚያን ዘመን ሰዎች ግን እነዚህን ሁሉ ለድኅነታቸው አልተጠቀሙባቸውም፤ ይልቁንም የተቀበሉትን ነገር ወደ ተቃራኒው ለወጡት።

ታዲያ ምን መደረግ ነበረበት? በግዴታና በኃይል ሊጎትታቸው ይገባ ነበርን? ይህማ ቢሆን ኖሮ በጎነት አይሆንም ነበር። ስለዚህ ከዚያ በኋላ የቀረው ብቸኛው መንገድ እርሱ እንዲተዋቸው ነበር፤ እርሱም እንዲህ አደረገ እግዚአብሔርም (እንዲተዋቸው ያደረገው) ቢያንስ በዚህ መንገድ፣ በሌላ ካልሆነ በምኞታቸው ምክንያት የሚመጣባቸውን መከራ በፈተና እንዲያውቁና ያን ያህል አሳፋሪ ከሆነው ነገር ይሸሹ ዘንድ ነው። ለምሳሌ የአንድ ንጉሥ ልጅ አባቱን አዋርዶ ከሌቦች፣ ከነፍሰ ገዳዮችና መቃብር ከሚቆፍሩ ሰዎች ጋር ለመሆን ቢመርጥ፣ የአባቱንም ቤት ቢንቅ፤ አባቱ ያን ልጅ ይተወዋል። ይኸውም በገዛ ድርጊቱ የሚመጣውን መከራ ቀምሶ የገዛ እብደቱን ይረዳ ዘንድ ነው።

ታዲያ (ጳውሎስ) እዚህ ጋር ሌሎችን ኃጢአቶች—ለምሳሌ ነፍሰ ገድያን ወይም ስግብግብነትን—ሳይጠቅስ ለምን ዝሙትንና ርኩሰትን ብቻ ጠቀሰ? ይህ የሆነው በወቅቱ የነበሩትን

ሰሚዎቹንና መልእክቱን የሚቀበሉትን ሰዎች ሁኔታ ለመጠቆም የፈለገ ይመስለኛል።

"እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ ወደ ርኩስነት... "እዚህ ጋር ቃሉ ያለውን ኃይልና ጥብቅነት ተመልከት። እነርሱን የሚያዋርዳቸው ሌላ ባዕድ አካል አላስፈለጋቸውም፤ ይልቁንም ጠላቶቻቸው ሊያደርጉባቸው የሚገባውን ግፍ እነርሱ ራሳቸው በራሳቸው ላይ ፈጸሙት። ከዚያም ክሱን እንደገና በማንሣት እንዲህ ይላል፦

ቁጥር ፳፭፦ "እግዚአብሔርንም ከማምለክ ይልቅ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ የእግዚአብሔርን እውነት በሐሰት ለወጡ። "

ፍጹም መሳለቂያና ውርደት የሆኑትን (የጣዖት አምልኮ ዓይነቶች) በዝርዝር ይገልጻቸዋል፤ ከሌሎቹ ይልቅ ከበድ ያሉ የሚመስሉትን ግን በጥቅል ቃላት ያስቀምጣቸዋል። በዚህም ፍጥረትን ማምለክ የአረማውያን (የግሪኮች) ተግባር መሆኑን ያሳያል። አነጋገሩም ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ ተመልከት፤ "ፍጥረትን አመለኩ" ብቻ ሳይሆን ያለው "ከፈጣሪ ይልቅ ፍጥረትን አመለኩ" ነው ያለው። በዚህም ንጽጽር ለሰዎቹ ምንም ዓይነት ማመካኛ እንዳይኖራቸው ያደርጋል።

"እርሱም (ፈጣሪ) ለዘላለም የተባረከ ነው፤ አሜን።"

በዚህ ቃል (ጳውሎስ) ሊያስተላልፍ የፈለገው፦ "እግዚአብሔር በእነርሱ ድርጊት ቅንጣት ታህል ጉዳት አልደረሰበትም" የሚል ነው። እርሱ በባሕርይው "ለዘላለም የተባረከ" ሆኖ ይኖራልና።

ይህም እግዚአብሔር እነርሱን የተዋቸው ራሱን ለመከላከል እንዳልሆነ ያሳያል፤ ምክንያቱም እርሱ ምንም ዓይነት ጉዳት አይደርስበትምና። እነርሱ በትዕቢት ቢንቁትም፣ እርሱ አልተናቀም፤ በክብሩም ላይ ምንም ዓይነት ጉድለት አልደረሰም፤ ይልቁንም ዘወትር የተባረከ ሆኖ ይኖራል።

ሰው እንኳ በጥበብ (በፍልስፍና) ከፍ ሲል ሰዎች የሚያደርሱበትን ስድብና ውርደት የማይሰማው ከሆነ (የማይበገረው ከሆነ)፤ የማይጠፋውና የማይለወጠው፣ የማይናወጥ ክብር ያለው የእግዚአብሔር ባሕርይማ እንዴት ይበልጥ የማይበገር አይሆንም! ሰዎችም ቢሆኑ፣ በሌሎች የሚደርስባቸውን በደል ባልተሰማቸው ጊዜ እግዚአብሔርን ይመስላሉ። ሌሎች ቢሰድቧቸው እንደማይሰደዱ፣ ቢመቷቸው እንደማይመቱ፣ ቢሳለቁባቸውም እንደማይሳለቅባቸው ሲሆኑ ማለት ነው።

አንድ ሰው "ታዲያ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ?" ሊል ይችላል። አዎን! በእርግጥ ይቻላል፤ ይህም የሚሆነው በሚደረግብህ ነገር ልብህ በማይጨነቅ (ባልተበሳጨህ) ጊዜ ነው። "ታዲያ አለመበሳጨት እንዴት ይቻላል?" ቢባል፤ እንዲያውም "ለምን ይበሳጫል?"ብሎ መጠየቅ ይሻላል። እስኪ ንገረኝ፦ ትንሽ ልጅህ ቢሰድብህ፣ ያንን ስድብ እንደ ስድብ ትቆጥረዋለህን? ወይስ ትበሳጫለህ? በእርግጥም አትበሳጭም። ብትበሳጭስ አንተ ራስህ መሳቂያ አትሆንም? እንግዲህ ለባልንጀሮቻችን እንዲህ ያለ ስሜት ይኑረን፤ ያን ጊዜ ቅሬታ አይሰማንም። ምክንያቱም እኛን የሚሰድቡን ሰዎች ከሕፃናት ይልቅ የማያስተውሉ ናቸውና። ከስድብ ነጻ ለመሆን አንፈልግ፤ ይልቁንም በተሰደብን ጊዜ በትዕግሥት ለመቀበል እንትጋ። ብቸኛውና አስተማማኙ ክብር

ይህ ነውና። ለምን? ምክንያቱም ለትዕግሥትህ አንተ ራስህ ጌታ ስትሆን፣ ለስድቡ ግን ሌላው ሰው ጌታ ነውና።

አልማዝ የሚመታውን ነገር እንዴት መልሶ እንደሚመታ (እንደማይበገር) አታይምን? ይህ በባሕርይው የተሰጠው ነው ትል ይሆናል፤ አንተ ግን በፈቃድህ እንዲህ መሆን ትችላለህ። እንዴት? በውኃ እቶን ውስጥ የነበሩት ሕፃናት እንዳልተቃጠሉ፣ ዳንኤልም በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ጉዳት እንዳልደረሰበት አታውቅምን? ይህ ዛሬም ሊሆን ይችላል። ዛሬም በዙሪያችን የሚቆሙ አንበሶች አሉ፤ እነርሱም ቊጣ እና ፍትወት ናቸው።

በእነርሱ መካከል የወደቀውን በክፉ ጥርሶቻቸው የሚቦጭቁ አስፈሪ አንበሶች! አንተ ግን እንደዚያኛው ዳንኤል ሁን፤ እነዚህ ስሜቶች ጥርሶቻቸውን በነፍስህ ላይ እንዲያሳርፉ አትፍቀድ። “ያ እኮ በጸጋ የተደረገ ነው” ትል ይሆናል፤ አዎን! ነገር ግን የራሱ የዳንኤል ፈቃድና ተግባር ለጸጋው መንገድ ጠርጓል። እኛም ራሳችንን ለእንዲህ ያለ ባሕርይ ካዘጋጀን፣ ዛሬም ጸጋው ቅርብ ነው። እነዚህ አራዊት (ስሜቶች) ቢራቡ እንኳ ጎንህን አይነኩትም።

አንበሶቹ የአገልጋዩን (የዳንኤልን) ሥጋ ባዩ ጊዜ ካፈሩ፤ የክርስቶስ ብልቶች የሆንነውን እኛን ምእመናን ባዩ ጊዜማ እንዴት ዝም አይሉም? ዝም የማይሉ ከሆነ ግን ጥፋቱ በእነርሱ መካከል በተጣለው ሰው (በእኛ) ነው። ብዙዎች ለእነዚህ አንበሶች (ለቊጣ እና ለፍትወት) ዝሙትን በመፈጸም፣ ትዳርን በመድፈርና ጠላትን በመበቀል ብዙ ቀለብ ይሰጧቸዋልና። በዚህም ምክንያት ወደ ጉድጓዱ ጥርሶች ሳይደርሱ ተበጣጥሰው ያልቃሉ። በዳንኤል ላይ ግን እንዲህ አልሆነም፤ እኛም ብንፈቅድ በእኛ ላይ አይሆንም።

እንዲያውም ከዚያ በላይ የሆነ ድንቅ ነገር ይከናወናል። አንበሶቹ ዳንኤልን አልጎዱትም፤ እኛም አስተዋዮች ከሆንን የሚጎዱን (የሚሰድቡን) ሰዎች እንኳ ይጠቅሙናል እንጂ አይጎዱንም።

ጳውሎስ የከበረው በተቃወሙትና በሴራ በከበቡት ሰዎች መካከል ነው፤ ኢዮብ የከበረው በብዙ መከራ ውስጥ ነው፤ ኤርምያስም በጭቃ ጉድጓድ ውስጥ፣ ኖኅ በማዕበል ውስጥ፣ አቤል በወንድሙ ክህደት ውስጥ፣ ሙሴ ደግሞ ደም መጣጭ በነበሩት አይሁድ መካከል ሆነው ነው የከበሩት። ኤልሳዕም ሆነ ሌሎች የቀደሙ ቅዱሳን ሁሉ የክብር አክሊላቸውን ያገኙት በምቾትና በለዘብተኝነት ሳይሆን፣ በመከራና በፈተና ውስጥ አልፈው ነው።

ለዚህ ነው ክርስቶስ ይህ (መከራ) የመልካም ምስክርነት መሠረት መሆኑን ስላወቀ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ያለው፦ “በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ” (ዮሐ. ፲፮÷፴፫)።" አንዳንዶች ግን፦ “ታዲያ ብዙዎች በእነዚህ መከራዎችና ፍርሐቶች ምክንያት ድል አልተነሱምን? (ወደ ኋላ አላፈገፈጉምን?) “ ይሉ ይሆናል። አዎን! ነገር ግን ይህ የሆነው በመከራው (በፈተናው) ባሕርይ ምክንያት ሳይሆን፣ በእነርሱ የራስ መዘናጋት እና ዳተኝነት ምክንያት ነው። “ከሚቻላችሁ በላይ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፤ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል” (፩ ቆሮ. ፲÷፲፫) ተብሎ እንደተጻፈ፤ እርሱ በሁላችንም አጠገብ ይቁም፤ እጁንም ይዘርጋልን።

እኛም በታላቅ ክብር ድል አድራጊዎች ተብለን እንድንታወቅና የዘላለም አክሊላትን እንድንወርስ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እና ሰው ወዳድነት፤ በእርሱ አማካኝነት እና ከእርሱ ጋር፣ ከመንፈስ ቅዱስም ጋር ለአብ ክብር ይሁን፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ፤ አሜን።"

# ድርሳን አራት (Homily IV )

(ሮሜ ፩፥፳፮-፳፯) ፦ "ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤"

እነዚህ ፍትወቶች (ምኞቶች) ሁሉ አስነዋሪዎች ነበሩ፤ በተለይም በወንዶች መካከል ያለው ያ እብደት የተሞላበት ፍትወት እጅግ የከፋ ነው። ምክንያቱም አካል በበሽታ እንደሚሰቃየው ሁሉ፣ ነፍስ በኃጢአት ይበልጥ ትሰቃያለች፣ ይበልጥም ትዋረዳለች።

ተመልከት! ሐዋርያው ስለ እምነት ትምህርት ሲናገር እንዳደረገው ሁሉ፣ እዚህም ላይ ስለ ሴቶቹ "ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለወጡ" በማለት ማመካኛ ያሳጣቸዋል። "ሕጋዊ የሆነውን ግንኙነት ስላጡ ወይም ፍላጎታቸውን የሚፈጽሙበት መንገድ ስለሌላቸው ወደዚህ አስከፊ እብደት ተገፋፉ" የሚል ማንም የለም ማለቱ ነው። ምክንያቱም "መለወጥ" የሚለው ቃል መጀመሪያ የነበረን ነገር መኖርን ያመለክታልና። ይህንኑ ሐሳብ ስለ እምነት ሲናገር "የእግዚአብሔርን እውነት በሐሰት ለወጡ" በማለት ገልጾት ነበር።

ስለ ወንዶችም ሲናገር "ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው" በማለት ያንኑ እውነት ያሳያል። እነዚህንም ቢሆን ምንም ዓይነት የመከላከያ መንገድ እንዳይኖራቸው ያደርጋል። ምክንያቱም የፍትወት ማርኪያ እያላቸው ያንን ትተው ወደ ሌላ በመሄዳቸው ብቻ ሳይሆን፣ ተፈጥሯዊ የሆነውን ነገር አዋርደው ከተፈጥሮ ውጪ ወደሆነው በመሮጣቸው ጭምር ይከሳቸዋል። ከተፈጥሮ ውጪ የሆነ ነገር ደግሞ በውስጡ አሰልቺነትና ደስታ ቢስነት አለበት፤ ስለዚህ "ደስታ አግኝተንበት ነው" የሚል ሰበብ እንኳ ማቅረብ አይችሉም። እውነተኛ ደስታ ከተፈጥሮ ጋር አብሮ የሚሄደው ነውና። እግዚአብሔር ሰውን ሲተወው ግን ሁሉም ነገር ተዘቅዝቆ ይገለበጣል። በዚህም ምክንያት እምነታቸው ሰይጣናዊ እንደነበረ ሁሉ ሕይወታቸውም ዲያብሎሳዊ ሆነ።

ሐዋርያው ስለ እምነት ትምህርት ሲያስተምር ዓለምንና የሰውን ማስተዋል በፊታቸው አቅርቦ ነበር፤ እግዚአብሔር በሰጣቸው የማስተዋል ችሎታ ከሚታዩት ፍጥረታት ተነስተው እንደ እጅ መሪ ወደ ፈጣሪ መድረስ ይችሉ እንደነበረና ይህን ባለማድረጋቸው ማመካኛ እንደሌላቸው ነግሯቸዋል። እዚህ ደግሞ በዓለም ፋንታ "ተፈጥሯዊ ደስታን" ያስቀምጣል። ይህንንም በተረጋጋና በደስተኛ መንፈስ ሊያጣጥሙትና ከአስነዋሪ ድርጊቶች ሊርቁ ይችሉ ነበር። እነርሱ ግን አልፈለጉም፤ ስለዚህ ከይቅርታ ክልል ውጭ ናቸው፤ በተፈጥሮ ላይም ስድብን ፈጽመዋል። ከዚህም ይበልጥ አሳፋሪው ነገር ከወንዶች ይበልጥ የሐፍረት (የነውር) ስሜት ሊኖራቸው የሚገባው ሴቶች እንኳ እንዲህ ያለውን ግንኙነት መፈለጋቸው ነገሩን ይበልጥ አሳፋሪ ያደርገዋል። እዚህ ጋር የጳውሎስ አስተዋይነት ሊደነቅ ይገባዋል፤ ምክንያቱም ሁለት ተቃራኒ

ነገሮችን በአንድነትና በጥንቃቄ ፈጽሟል። ጳውሎስ ሐሳቡን በንጽህና መግለጽም፣ ሰሚውንም ማሳመምና መውቀስም ፈልጎ ነበር። እነዚህን ሁለት ነገሮች በአንድ ላይ ማድረግ ግን አስቸጋሪ ነው፤ አንዱ ሌላውን ይጋፋዋልና። በንጽህና (በተሸፋፈነ ቃል) ከተናገርክ ሰሚውን በደንብ ልትወቅሰው አትችልም፤ ነገር ግን ሰሚውን ልቡ ድረስ ዘልቆ እንዲሰማው ለማድረግ ከፈለግህ ደግሞ እውነታውን ያለ መጋረጃ በግልጽ ቃላት ለመዘርዘር ትገደዳለህ። የጳውሎስ አስተዋይነት እና ቅድስት ነፍስ ግን ሁለቱንም በጥንቃቄ ማድረግ ቻለች። “ተፈጥሮ” የሚለውን ቃል በመጥቀስ ክሱን ኃይለኛ እንዲሆን ሲያደርግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው “ተፈጥሮ የሚለው ቃል መግለጫውን በንጽህና ለመሸፈን እንደ መጋረጃ ሆኖለታል። በመጀመሪያ ሴቶችን ከወቀሰ በኋላ፣ ወደ ወንዶቹም በመመለስ “እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው” ይላል። ይህ ደግሞ የብልሽቱ መጨረሻ ደረጃ መሆኑን ግልጽ ማስረጃ ነው፤ ሁለቱም ጾታዎች በጠፉ ጊዜ፣ ሴቲቱን እንዲያስተምር የተሾመው ወንድና ለወንዱ ረዳት ትሆን ዘንድ የታዘዘችው ሴት እርስ በርሳቸው እንደ ጠላት ሲተያዩና እንደ ጠላት ሲደራረጉ ማየት እንዴት ያለ ጥፋት ነው!ቃላቱንም እንዴት ባለ ትርጉም እንደሚጠቀምባቸው ልብ በል። እርስ በርሳቸው ተዋደዱ ወይም ተመኙ አላለም፤ ይልቁንም “እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ” ነው ያለው። ፍትወት (ምኞት) ሁሉ ከተገቢው ገደብ ማለፍ እንደሚመጣ ተመልከት። በእግዚአብሔር የተሾሙትን ሕጎች የሚጥስ ሁሉ፣ የተለመዱትን ነገሮች ትቶ አስደንጋጭና ያልተለመዱ ነገሮችን ይመኛል። ብዙ ሰዎች የተለመደውን ምግብ ትተው አፈርና ትናንሽ ድንጋዮችን ለመብላት እንደሚመኙ፣ ሌሎች ደግሞ ከፍተኛ ጥም ሲይዛቸው

ጭቃማ ውኃን እንደሚመኙ ሁሉ፤ እነዚህም ወደዚህ ሕገ-ወጥ የፍቅር እሳቤ ውስጥ ገቡ።

"ይህ ሁሉ የፍትወት ጥንካሬ ከየት መጣ?" ብትል፤ እግዚአብሔር ሰውን በመተዉ ምክንያት የመጣ ነው።

"እግዚአብሔርስ ለምን ተዋቸው?" ብትል፤ እርሱን ትተው ወደ ሕገ-ወጥነት ስለገቡ ነው። "ወንዶች በወንዶች ላይ የሚያሳፍር ሥራ እየሠሩ" ይላል። "ተቃጠሉ" የሚለውን ስትሰማ ክፋቱ በምኞት ብቻ ያለ እንዳይመስልህ፤ ትልቁ ጥፋት የመጣው ከቅንጦታቸው የተነሳ ሲሆን እርሱም ፍትወታቸውን እንደ እሳት አቀጣጠለው። ለዚህም ነው በሌላ ቦታ እንደሚለው "ተወሰዱ"ወይም "ተያዙ" ሳይሆን "የሚያሳፍር ሥራ እየሠሩ" ያለው። ኃጢአቱን እንደ ሥራ አደረጉት፤ ሥራ ብቻም ሳይሆን በቅንዓት የሚከተሉት ተግባር አደረጉት።

"ፍትወት" አላለውም ይልቁንም "የሚያሳፍር ሥራ" አለው፤ ይህም ተገቢ ስያሜ ነው። ምክንያቱም ተፈጥሮን አዋርደዋል፣ ሕግጋትንም ረግጠዋልና። በሁለቱም ወገን የታየውን ታላቅ ግራ መጋባት ተመልከት። ራሱ ወደ ታች ተዘቅዝቆ የተደፋ ብቻ ሳይሆን፣ እግሩም ወደ ላይ የወጣ ሆነ፤ ለራሳቸውና እርስ በርሳቸውም ጠላት ሆኑ ይህ ዓይነቱ ግጭት ከማንኛውም የእርስ በርስ ጦርነት ይልቅ እጅግ ጎጂና ሕገ-ወጥ ነው፤ በውስጡም ልዩ ልዩ የሆኑ መከፋፈሎችን የያዘ ነው። ይህንን ጦርነት አዳዲስና ሕገ-ወጥ መንገዶች ከፍለውታል። ምክንያቱም ይህ ጦርነት ሁለት ወይም ሦስት እጥፍ ብቻ ሳይሆን አራት እጥፍ ነውና። እስኪ አስብ! ወንድና ሴት አንድ ሊሆኑ ይገባ ነበር፤ "ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ" (ዘፍ. ፪፥፳፬) ተብሏልና። ይህንንም አንድነት

የሚፈጥረውና ጾታዎችን እርስ በርሳቸው የሚያስተሳስረው የፍላጎት ዝንባሌ ነበር። ዲያብሎስ ግን ይህንን ፍላጎት ወስዶ ወደ ሌላ አቅጣጫ በማዞር ጾታዎችን እርስ በርሳቸው ለያያቸው፤ ከእግዚአብሔር ሕግ በተቃራኒም አንድ የነበረውን ወደ ሁለት ተቃራኒ ክፍሎች ለወጠው። ሕጉ "ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ" ቢልም፣ እርሱ ግን አንድ የነበረውን ሥጋ ለሁለት ከፈለ—ይህ አንደኛው ጦርነት ነው።

ደግሞም እነዚህኑ ሁለት ወገኖች በገዛ ራሳቸውና እርስ በርሳቸው እንዲጣሉ አደረገ። ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችም በሴቶች ላይ ነውርን ፈጸሙ። ወንዶችም እርስ በርሳቸውና በሴቶች ላይ ተነሱ፤ ይህም ልክ በጨለማ እንደሚደረግ ውጊያ ነው። እዚህ ጋር ሁለተኛ፣ ሦስተኛ፣ አራተኛና አምስተኛ ጦርነትን ታያለህ። ሌላው ደግሞ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በተፈጥሮ ላይ የፈጸሙት ሕገ-ወጥ ተግባር ነው። ዲያብሎስ ጾታዎችን የሚያገናኘው ዋነኛው ትስስር ይህ ፍላጎት መሆኑን ባየ ጊዜ፣ ያንን ትስስር ለመበጠስ ቆረጠ። ይህንንም ያደረገው የሰውን ዘር ለማጥፋት ሲል ነው፤ ይህም በሕጋዊ መንገድ እንዳይዋለዱ በማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ እርስ በርሳቸው በጦርነት እና በሁከት እንዲነሳሱ በማድረግ ጭምር ነው።

"ለስሕተታቸውም የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።"
ተመልከት! ሐዋርያው እንደገና ወደ ክፋቱ ምንጭ ይመለሳል፤ ይህም ከእምነታቸው የመጣው ክህደት ነው። ይህ (የሥጋ ርኩሰት) ለዚያ ሕገ-ወጥነት የተሰጠ ዋጋ (ብድራት) ነው ይላል። ለገዛ ፈቃዳቸው ለሚገዙና እንዲህ ያለውን ሕይወት ለሚመርጡ ዓመፀኞች ስለ ገሃነም ቢነግራቸው አሁን ላይ ላያምኑ ወይም ሊያፌዙ ስለሚችሉ፣ ቅጣቱ በዚሁ "ደስታ" ውስጥ እንዳለ

ያሳያቸዋል። በዚህ ድርጊት ውስጥ ሆነው ሳለ ምንም ካልተሰማቸውና አሁንም ደስተኞች ከሆኑ አትደነቅ። ምክንያቱም አእምሮአቸውን የሳቱና በዕብደት የተመቱ ሰዎች በራሳቸው ላይ ብዙ ጉዳት እያደረሱ፣ ሌሎች ስለ እነርሱ እያለቀሱላቸው ሳለ፣ እነርሱ ግን በሆነው ነገር ላይ ፈገግ ይላሉ፣ ይደሰታሉም።

እኛ ግን በዚህ ምክንያት ከቅጣት ነፃ ናቸው አንልም፤ ይልቁንም ያሉበትን አስከፊ ሁኔታ ባለማወቃቸው ቅጣታቸው ይበልጥ የከፋ እንደሆነ እንረዳለን። የአንድን ነገር ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የታመሙትን ሳይሆን ጤነኞቹን መጠየቅ ይገባልና። በቀድሞ ዘመን ግን ይህ ድርጊት እንደ ሕግ ይታይ ነበር፤ በመካከላቸውም የነበረ አንድ ሕግ ሰጪ (ሊኩርገስ) የቤት ባሪያዎች ቅባት እንዳይቀቡ ወይም ከወጣቶች ጋር ዝምድና እንዳይኖራቸው ይከለክሉ ነበር፤ ይህንን "የክብር ቦታ" (እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የውርደት ቦታ ነው) ለጨዋዎች (ለነፃ ሰዎች) ብቻ ይሰጡ ነበር። ይሁን እንጂ እነርሱ ይህንን ነገር እንደ ነውር ሳይሆን፣ ለባሪያዎች የማይገባ ታላቅ መብት አድርገው ይቆጥሩት ነበር። የጥበብ ሰዎች መገኛ የምትባለው የአቴና ሕዝብና በመካከላቸው ትልቅ ክብር ያለው ሶሎን እንኳ ይህንን ድርጊት ለነፃ ሰዎች ብቻ ፈቅደው ነበር። በሌሎችም የፈላስፎች መጻሕፍት ውስጥ ይህ በሽታ ሞልቶ ይገኛል[5]።

---

[5] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በጥንቷ ግሪክና ስፓርታ የነበሩትን ሕጎች በመጥቀስ፣ በወቅቱ የነበሩ ፈላስፎችና ሕግ አውጪዎች ይፈጽሙት የነበረውን ነውር ያጋልጣል። በጥንቷ ስፓርታ ታዋቂ የነበረው ሕግ አውጪ ሊኩርጎስ (Lycurgus) ያወጣው ሕግ፣ የቤት ባሪያዎች ሰውነታቸውን በዘይት እንዳይቀቡ (ይህ የንጽህናና የጂምናዚየም ስፖርት መብትን ያመለክታል) እና ከነጻ ወጣቶች ጋር ፍቅራዊም ሆነ ወሲባዊ ዝምድና እንዳይኖራቸው ይከለክል ነበር። ይህንን ድርጊት ወይም «የክብር ቦታ» የሚፈቅደው ለነጻ ዜጎች ብቻ ነበር። ሊቁ በቅንፍ እንደገለጸው፣ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ፊት እጅግ የውርደትና የኃጢአት ቦታ ቢሆንም፣ እነርሱ ግን ለባሪያዎች የማይገባ ታላቅ መብትና ክብር አድርገው ይቆጥሩት ነበር።
ይባስ ብሎም በጥበባቸውና በፍልስፍናቸው በዓለም ላይ የሚደነቁት የአቴንስ ሕዝቦችና ታዋቂው ፈላስፋ ፕላቶ (በጽሑፉ ላይ 'ሰሎን' ወይም 'ፕላቶ' በሚለው ስም የተጠቀሰው) በጻፏቸው የሕግና የፍልስፍና መጻሕፍት ውስጥ ይህንን ነውርና «በሽታ» እንደ ሥርዓት ፈቅደውትና ሞልቶበት ይገኛል። ሊቁ ይህንን ታሪክ ያመጣው፣ የዓለም ፈላስፎችና ሕግ አውጪዎች ያለ ወንጌል ብርሃን የደረሱበት የሞራል ውድቀት ምን ያህል የከፋ እንደነበርና የሰው ልጅ ጥበብ ራሷ በዝሙትና በነውር በሽታ የተሞላች መሆኗን ለአንባቢው ለማሳየት ነው።


ታሪካዊ ማጣቀሻዎች (Historical References):

ሊኩርጎስ (Lycurgus of Sparta): የክላሲካል ታሪክ ጸሐፊው ፕሉታርክ (Plutarch) «የሊኩርጎስ ሕይወት» (*Life of Lycurgus*) በሚለው መጽሐፉ ላይ፣ በስፓርታ ሕግ ባሪያዎች (Helots) ስፖርት ከሚሰራባቸው ቦታዎች (Gymnasia) እንዲታገዱ እና የተወሰኑ ማኅበራዊ መብቶች ይከለከሉ እንደነበር ይዘግባል።
የፕላቶ መጻሕፍት (Plato's Dialogues): ፕላቶ «Laws» (ሕጎች) እና «Symposium» በተባሉ ታዋቂ የፍልስፍና መጻሕፍቱ ውስጥ በጥንቷ ግሪክ ይሠራበት የነበረውን ይህንን ማኅበራዊ ነውርና ግንኙነት በሰፊው ይተነትናል።

ነገር ግን እኛ በዚህ ምክንያት ድርጊቱ “ሕጋዊ” ነው አንልም፤ ይልቁንም እንዲህ ያለውን ሕግ የተቀበሉ ሰዎች እጅግ የሚያሳዝኑና ብዙ እንባ የሚገባቸው ናቸው እንላለን። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች እንደ ጋለሞታ ሴቶች ነው የሚቆጠሩት። እንዲያውም የእነርሱ ሁኔታ ይባስኑ የከፋ ነው። በጋለሞታይቱ ዘንድ ግንኙነቱ ሕገ-ወጥ ቢሆንም እንኳ ከተፈጥሮ ጋር የሚስማማ ነው፤ ይህኛው ድርጊት ግን ሕግንም ተፈጥሮንም የሚጻረር ነው። ምናልባት ገሃነም ባይኖርና ምንም ዓይነት ቅጣት ባንቀጣም እንኳ፣ ይህ ድርጊት ከማንኛውም ቅጣት ይልቅ የከፋ ነው። “በውስጡ ደስታ አገኙበት”ብትለኝ፣ ይህማ ቅጣቱን ይበልጥ የሚያከብድ (የሚጨምር) ነገር ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ራቁቱን እየሮጠ፣ ሰውነቱ በጭቃ ተለጥፎ፣ ራሱን ከመሸፈን ይልቅ በዚያው ሲመካና ሲደሰት ባየው፣ ከእርሱ ጋር ደስ አይለኝም፤ ይልቁንም እንዲህ ያለ አሳፋሪ ነገር እያደረገ መሆኑን እንኳ ባለማወቁ ይበልጥ አለቅስለታለሁ።

ይህንን ግፍ ይበልጥ ግልጽ በሆነ ብርሃን አሳይህ ዘንድ አንድ ተጨማሪ ምሳሌ ልስጥህ። አንድ ሰው አንዲት ድንግልን በጠባብ ዋሻ ውስጥ እንድትኖርና አእምሮ ከሌላቸው አራዊት ጋር ግንኙነት እንድትፈጽም ቢፈርድባት፣ እርሷም በዚያ ግንኙነት ደስተኛ ብትሆን፤ ያለችበትን መከራ ባለማወቋ ብቻ ከዚያ መከራ ነፃ መውጣት ስለማትችል ይበልጥ ልናዝንላት አይገባም ነበርን? ይህ ለማንኛውም ሰው ግልጽ ነው። ታዲያ ያ (ከአራዊት ጋር መኖር) አሰቃቂ ነገር ከሆነ፣ ይህኛው ድርጊት ከእርሱ በምንም አያንስም። ምክንያቱም በገዛ ወገኖችህ መጠቃት ከማያውቁህ ሰዎች ከመጠቃት ይልቅ ይበልጥ የሚያሳዝን ነውና። እነዚህ ሰዎች (ይህንን ድርጊት የሚፈጽሙት) ከነፍሰ ገዳዮች እንኳ ይብሳሉ

እላለሁ፤ ምክንያቱም እንዲህ ባለ ውርደት ከመኖር መሞት ይሻላልና። ነፍሰ ገዳይ ነፍስን ከሥጋ ይለያል፤ ይህ ሰው ግን ነፍስን ከሥጋ ጋር አብሮ ያጠፋታል። ከዚህ ሕገ-ወጥነት ጋር የሚተካከል ምንም ዓይነት ኃጢአት ልትጠቅስ አትችልም። ይህ መከራ የሚደርስባቸው ሰዎች (ተገዳጅ የሆኑት) ያለባቸውን ጉዳት ቢያውቁ ኖሮ፣ ይህ ክፉ ነገር እንዳይደርስባቸው አሥር ሺህ ጊዜ መሞትን በመረጡ ነበር።

ከዚህ አሳፋሪ ግፍ የበለጠ ከባድ ክፉ ነገር የለምና። ጳውሎስ ስለ ዝሙት ሲናገር፦ "ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአት ይሠራል" (፩ ቆሮ. ፮፥፲፰) ካለ፤ ከዝሙት እጅግ ለሚከፋውና በቃል ሊገለጽ ለማይችለው ለዚህ እብደት ምን እንላለን? አንተ ሴት ሆነሃል ብቻ አልልም፤ ይልቁንም ወንድነትህን አጥተሃል፣ ወደዚያኛው (ወደ ሴትነት) ባሕርይ አልተለወጥህም፣ የነበረህንም (ወንድነትን) አልጠበቅህም በአንድ ጊዜ ለሁለቱም (ለወንድነትህም ለሴትነትም) ከዓተኛ ሆነሃል፤ ሁለቱንም ጾታዎች በድለሃልና በወንዶችም በሴቶችም ዘንድ ልትገለልና ልትወገር ይገባሃል። የዚህን ድርጊት እውነተኛ አስከፊነት ትረዳ ዘንድ ይህንን አስብ፦ አንድ ሰው መጥቶ "ከሰውነት አውጥቼ ውሻ አደርግሃለሁ" ቢልህ፣ እንደ መቅሰፍት ቆጥረህ ከእርሱ ባልሸሸህ ነበርን? ነገር ግን እነሆ! አንተ ራስህን ከሰውነት ወደ ውሻነት ሳይሆን፣ ከውሻም ወደሚብስ አሳፋሪ እንስሳነት ለውጠሃል። ውሻ እንኳ ለጥቅም (ለአገልግሎት) ይውላል፤ በዚህ ድርጊት ራሱን አሳልፎ የሰጠ ግን ለምንም ነገር አይጠቅምም።

ወይም ደግሞ አንድ ሰው ወንዶችን “አምጣችሁ እንድትወልዱ አደርጋችኋለሁ” ብሎ ቢዝትብን፣ በታላቅ ቁጣ ባልተሞላን ነበርን? ነገር ግን እነሆ! ወደዚህ እብደት የገቡት በገዛ ራሳቸው ላይ ከዚያ የከፋ ነገር አድርገዋል። ወደ ሴትነት ባሕርይ መለወጥና ወንድ ሆነህ ሳለ ሴት ለመሆን መሞከር አንድ አይደለም፤ እንዲያውም ይህኛው ከዚያም ይብሳል። የዚህን ክፋት ግዙፍነት ከሌላ አቅጣጫ ማወቅ ከፈለግህ፤ ሕግ አውጪዎች ሰውን ጃንደረባ የሚያደርጉትን (የሚሰልቡትን) ለምን እንደሚቀጡ ጠይቅ።

ለዚህም ብቸኛው ምክንያት ተፈጥሮን ስለሚያበላሹ መሆኑን ትረዳለህ። ነገር ግን እነርሱ የሚፈጽሙት ግፍ ከዚህኛው ጋር ሲነጻጸር ምንም አይደለም። ምክንያቱም የተሰለቡ ሰዎች ከተሰለቡ በኋላም ለብዙ ነገር ጠቃሚ የሚሆኑበት አጋጣሚ አለና። ራሱን ለዝሙት አሳልፎ የሰጠ (ያረከሰ) ሰው ግን ከእርሱ የሚበልጥ የማይረባ ፍጥረት የለም። የዚህ ድርጊት ሰለባ የሆነው ሰው ነፍሱ ብቻ ሳይሆን ሥጋውም ይረክሳል፤ በሁሉም ቦታ ሊገለልም ይገባዋል። ለእንዲህ ያለ ሰው ስንት ገሃነም ይበቃዋል? ስለ ገሃነም ስትሰማ የምታፌዝ ከሆነና ያንን እሳት የማታምን ከሆነ፣ የሰዶምን ጥፋት አስታውስ። እኛ በእውነት በዚህ በምድራዊ ሕይወት እንኳ የገሃነምን አምሳያ አይተናልና። ብዙዎች ከትንሣኤ በኋላ የሚመጣውን ነገር ፈጽሞ ስለማያምኑ፣ አሁን የማይጠፋውን እሳት ሲሰሙ እግዚአብሔር በአሁኑ (በሚታየው) ነገር ወደ ልባቸው ይመልሳቸዋል።

የሰዶም ቃጠሎና ያ ውድመት እንዲህ ያለ ነው። ያንን ቦታ የረገጡና ያንን መለኮታዊ መቅሰፍት፣ ከላይ የወረደውንም የመብረቅ ውጤት በዓይናቸው ያዩ ሁሉ ይህን በሚገባ ያውቃሉ።

(ይሁዳ ፯)። ገሃነም ጊዜው ሳይደርስ አስቀድሞ እንዲገለጥ ያስገደደ ያ ኃጢአት ምንኛ ታላቅ እንደሆነ አስተውል! ብዙዎች የእግዚአብሔርን ቃል ንቀው ስለነበር፣ እግዚአብሔር በድርጊቱ የገሃነምን ምስል በአዲስ መንገድ አሳያቸው። ያ ዝናብ የተለመደ ዝናብ አልነበረም፤ ምክንያቱም ግንኙነታቸው ከተፈጥሮ ውጪ ነበረና፤ ፍትወት ነፍሳቸውን እንዳጥለቀለቃት ሁሉ ያ (የእሳት) ዝናብም ምድሪቱን አጥለቀለቃት። ለዚህም ነው ያ ዝናብ ከተለመደው ዝናብ ተቃራኒ የሆነው። ያ ዝናብ የምድርን ማህፀን አነቃቅቶ ፍሬ እንዲያፈራ ከማድረግ ይልቅ፣ ምድሪቱ ዘርን ለመቀበል እንኳ የማይጠቅም አደረጋት። የወንዶቹም ግንኙነት እንዲህ ነበር፤ አካላቸውን ከሰዶም ምድር ይልቅ የማይረባ አደረገው። ራሱን ካረከሰ ሰው ይበልጥ አጸያፊና የተጠላ ምን አለ? ኦ! ምን ዓይነት እብደት ነው! ኦ! ምን ዓይነት መቅለብለብ! ይህ ፍትወት እንዲህ ባለ አጸያፊ ሁኔታ  የሰውን ባሕርይ ጠላቶች ሊያደርጉት ከሚችሉት በላይ እንዲያሽቆለቁል አደረገው፤ እንዲያውም ነፍስ ከሥጋ እንደምትበልጥ ሁሉ ይህ ጥፋትም ከዚያ የከፋ ነው። እናንተ አእምሮ ከሌላቸው ፍጥረታት ይልቅ ማስተዋል የጎደላችሁ፣ ከውሾችም ይልቅ ሐፍረት የሌላችሁ! ምክንያቱም በእነርሱ ዘንድ እንኳ እንዲህ ያለ ግንኙነት ፈጽሞ አይደረግም፤ ተፈጥሮ የገዛ ገደቧን ታውቃለችና። እናንተ ግን እርስ በርሳችሁ በምትፈጽሙት እንዲህ ያለ ውርደት የሰውን ዘር ከአራዊት በታች አዋረዳችሁት።

ታዲያ እነዚህ ክፉ ነገሮች ከምን ተወለዱ? ከቅንጦትና እግዚአብሔርን ካለማወቅ ነው። አንድ ሰው እግዚአብሔርን መፍራት ከተወ፣ በጎ የሆነው ነገር ሁሉ ወዲያውኑ ወደ ጥፋት ይሄዳል። እንግዲህ ይህ እንዳይደርስብን፣ የእግዚአብሔርን ፍርሃት

ዘወትር በዓይናችን ፊት እናኑር። ሰውን እንደዚህ መልህቅ (እግዚአብሔርን መፍራት) የሚጥለውና የሚያጠፋው ምንም ነገር የለም፤ እንደዚሁም ዘወትር ወደ እርሱ እንደ መመልከት የሚያድን ነገር የለም። አንድ ሰው በፊታችን ሲኖር ኃጢአት ለመሥራት የምንሰቀቅ ከሆነ፣ ይልቁንም የተሻለ ግብረ-ገብነት ያላቸው አገልጋዮች ባሉበት ጥፋት ከመሥራት የምንቆጠብ ከሆነ፤ እግዚአብሔርን ዘወትር በዓይናችን ፊት ብናደርገው ምን ያህል ሰላምና ጥበቃ እንደምናገኝ አስብ! እንዲህ ባለው ሁኔታ ላይ ስንሆን ዲያብሎስ ፈጽሞ አያጠቃንም፤ ጥቃቱም ያለ ትርፍ እንደሚሆን ያውቃልና።

ነገር ግን ያለ ልጓም ስንቅበዘበዝ ካየን፣ በእኛ ላይ መግቢያ ቀዳዳ ያገኝና ወደ ፈለገበት ሊነዳን ይችላል። ልክ በገበያ ላይ እንዳሉ ግድ የለሽ አገልጋዮች፣ ጌቶቻቸው የሰጧቸውን አስፈላጊ ሥራ ትተው መንገድ ላይ ከሚያገኟቸው ሰዎች ጋር ለከንቱ ወሬ እንደሚቆሙና ጊዜያቸውን እንደሚያባክኑ፤ እኛም የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ስንተው እንዲህ ያለ ነገር ይደርስብናል። ወዲያውኑም ከእኛ ጋር የማይገናኙትን እንደ ባለጠግነት፣ የሰው ውበትና መሰል ከንቱ ነገሮችን ስናደንቅ እንቆማለን። እነዚህ አገልጋዮች አስማት የሚያሳዩ ለማኞችን እያዩ እንደሚዘገዩና በኋላም ቤታቸው ሲመለሱ በጌቶቻቸው እንደሚገረፉ ሁሉ፤ ብዙዎችም እንዲህ ያለውን አሳፋሪ መንገድ የሚከተሉትን ሰዎች እያዩ የተሰጣቸውን የሕይወት ጎዳና ይስታሉ።

እኛ ግን እንዲህ አናድርግ። እኛ እጅግ አስቸኳይ የሆኑ ብዙ ጉዳዮችን እንድንፈጽም ተልከናልና። እነዚያን ትተን እነዚህን የማይረቡ ነገሮች አፋችንን ከፍተን የምናይ ከሆነ፣ ጊዜያችን ሁሉ በከንቱ ይባክናል፤ መጨረሻውም ከባድ ቅጣት ይሆናል። ሥራ

መያዝ (busy መሆን) ከፈለግህ፣ ዕድሜህን ሙሉ ብታደንቃቸውና ብታስባቸው የማይሰለቹ፣ ለሳቅ ሳይሆን ለድንቅና ለብዙ ምስጋና የሚሆኑ ታላላቅ ነገሮች (መለኮታዊ ምስጢራት) በፊታችን አሉ። የማይረቡ ነገሮችን የሚያደንቅ ሰው ራሱ የማይረባ ይሆናል፤ እንዲያውም ለሳቅ ምክንያት ከሚሆነው ሰው ይልቅ እርሱ ይብሳል። ወደዚህ እንዳትወድቅ አሁኑኑ ርቀህ ሽሽ። ለመሆኑ ባለጠግነትን ስታይ ለምን እንዲህ ትክለፈለፋለህ? የምታየውስ ምንድነው? ለመሆኑ በሀብታሞች ዘንድ የምታየውና ዓይንህን የሚስበው ምን ድንቅ ነገር አለ?

በወርቅ የተለጉ ፈረሶቻቸው? እነዚህ አሽከሮቻቸው? ወይስ ግማሾቹ አረመኔ ግማሾቹ ደግሞ ጃንደረባ የሆኑት ገረዶቻቸው? ወይስ ውድ ልብሶቻቸውና በዚህ ሁሉ መሐል ፈዝዛ የምትቀረው ነፍሳቸው? ወይስ የኩራት ቁልቁል እይታቸው፣ ሽክሽካቸውና ጫጫታቸው? እነዚህ ነገሮች በምን መስፈርታቸው ነው ድንቅ የሚባሉት? በገበያ ውስጥ እየጨፈሩ እና ዋሽንት እየነፉ ከሚለምኑት ለማኞች በምን ይሻላሉ? እነዚህም (ባለጠጎቹ) በበጎነት ረሃብ ስለተመቱ፣ ከእነዚያ ለማኞች ይልቅ እጅግ አስቂኝ የሆነ ጭፈራ ይጨፍራሉ። አንድ ጊዜ ወደ ተንጣለለ ማዕድ፣ ሌላ ጊዜ ወደ ጋለሞታዎች ቤት፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ አታላዮችና ጥገኛ አጎብጓቢዎች መንጋ ይነዳሉ። ወርቅ ቢለብሱ እንኳ ይበልጥ ሊታዘንላቸው ይገባል፤ ምክንያቱም ለእነርሱ ምንም የማይጠቅሟቸውን ነገሮች አጥብቀው ይመኛሉና።እባክህን ልብሳቸውን አትመልከት፤ ይልቁንም ነፍሳቸውን ገልጠህ እይ! ነፍሳቸው ቁጥር በሌላቸው ቁስሎች የተሞላች፣ በጨርቅ የተጠቀለለች (የመነመነች)፣ ባዶዋን የቀረችና መከላከያ የሌላት መሆኑን አታይምን? ታዲያ እንዲህ ያለ የይስሙላ እብደት

ጥቅሙ ምንድነው? በክፋት ውስጥ ሆኖ ንጉሥ ከመሆን ይልቅ፣ በበጎነት ውስጥ ሆኖ ድሃ መሆን እጅግ ይሻላልና። ምክንያቱም ድሃው በውስጡ በነፍስ ደስታ ይረካል፤ በውስጣዊ ሀብቱ የተነሳም ውጫዊ ድህነቱ አይታወቀውም። ንጉሡ ግን የእርሱ ባልሆኑት(በምድራዊ ሀብቱ) እየተቀናጣ ሳለ፣ የእርሱ በሆኑትና ከእርሱ ጋር ወደ ወዲያኛው ዓለም በሚሄዱት—ማለትም በነፍሱ፣ በሐሳቡና በሕሊናው—ይቀጣል። እንግዲህ እነዚህን ነገሮች ካወቅን፣ በወርቅ የተለበጠውን ልብስ ወደ ጎን እንተው፤ በጎነትንና ከእርሷ የሚገኘውን ደስታ እንያዝ። በዚህም እዚህም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ታላቅ ደስታን እናገኛለን።

ይህም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰው ወዳድነት የሚሆን ነው፤ በእርሱ በኩል፣ ከእርሱም ጋር፣ ከመንፈስ ቅዱስም ጋር፣ ለአብ ክብር ይሁን፣ ለዘላለሙ፣ አሜን።"